# የቱሪዝም ዘርፍ የ2018 ዓ.ም ስትራቴጅክ አቅድ

## ቱሪዝም ሚኒስቴር

ነሃሴ 2017 ዓ.ም

## ማውጫ


መግቢያ ........ 2

1. የሴክተሩ ተልዕኮ፣ ራዕይና እሴቶች ........ 3

2. በ2017 በጀት ዓመት በአፈፃፀም ሂደት የታዩ መልካም ተሞክሮዎች፣ ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ........ 3

3. የእቅዱ ታሳቢዎች ........ 7

4. የትኩረት መስኮች፣ ስትራቴጅካዊ አቅጣጫዎችና ግቦች ........ 12

4.1 የትኩረት መስኮች ........ 12

4.2 የ2017 ስትራቴጅካዊ ግቦች ........ 12

4.3 ዋና ዋና ተግባራትና የሚጠበቁ ቁልፍ ውጤቶች ........ 12

5. ስትራጅካዊ ግቦች፣ ዋና ተግባራት፣ ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾችና ዒላማዎች ........ 23

6. የእቅዱ ማስፈፀሚያ ስልቶች ........ 35

6.1 የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ........ 36

6.2 የግምገማና ግብረ መልስ ሥርዓት ........ 37

## መግቢያ

አገራችን ፈርጀ-ብዙ የቱሪዝም ሃብቶች ባለቤት ብትሆንም ዘርፉን በሚገባ አልምቶ ተገቢውን ኢኮኖሚያ ጥቅም እንዲያመነጭ ከማድረግ አኳያ ሰፊ ክፍተቶች አሉ፡፡ በአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ (Homegrown Economic Reform) ውስጥ ልዩ ትኩረት ከተሰጣቸው አምስቱ የኢኮኖሚ መሰረቶች ውስጥ አንዱ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በዚህም የሀገሪቱ እምቅ የቱሪዝም መልማት አቅም ለኢኮኖሚ እድገት አሟጦ ለመጠቀም እንዲቻል የማህበራዊ አስተዋፅኦ እንደተጠበቀ ሆኖ በአሥር አመት መሪ የልማት እቅድ ውስጥ የቱሪዝም ኢኮኖሚያዊ ድርሻ ጎልቶ እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለዘርፉ ፈጣን እድገት ዋስትና የሚሆኑ ሞዴል የመዳረሻ ልማት ፕሮጀክቶች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተግባራዊ ሆኗል፡፡ እንዲሁም ቱሪዝም በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ራሱን ችሎ በሚኒስቴር መስሪያ ቤት ደረጃ ከተደራጀ ወዲህ ለዘርፉ እድገት ማነቆ የሆኑ ልማዳዊ አሰራሮች በመፈተሽ የተለያዩ የህግ ማዕቀፍ ማሻሻያ ስራዎች ተከናውኗል፡፡

ዘርፉ የሀገራችን "የአፍሪካ የብልፅግና ተምሳሌት" የመሆን ርዕይ ለማሳካት የተጣለበትን ትልቅ ተስፋ እውን እንዲሆን እስካሁን በዘርፉ የተገኙት ውጤቶች አበረታች ቢሆንም ሀገራችን ካላት እምቅ የመልማት አቅም ጋር ሲነጻጸር አሁንም ችግሮች የሚስተዋሉበት፣ ፍትሃዊ የማልማትና የማስተዋወቅ ስራ የተጀመረበት፣ በቅርቡ አዲስ አደረጃጀት የተፈተረለት እና በአጠቃለይ ከሚጠበቅበት አንጻር ብዙ መራመድ የሚጠበቅበት ሴክተር ነው፡፡

የአስር ዓመቱን እቀድ መንዝሮ ተግበራዊ ለማድረግ የሚያስችል የመካከለኛ ዘመን (2016-2018) እቅድ ተዘጋጅቶ በዘርፉ በርካታ ስራዎች በመከናወን ላይ ናቸው፡፡ በ2017 በጀት 007ዓመት የዘርፉን የመካከለኛ ዘመን ዒላማዎች ለማሳካት የሚያስችሉ አንኳር ስራዎች የሚከናወንበት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ስለሆነም ይህ ዓመታዊ እቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

## 1. የሴክተሩ ተልዕኮ፣ ራዕይና እሴቶች

### ተልዕኮ

የአገራችን ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ የቱሪዝም ሃብቶች በማጥናት፣ በህብረተሰቡ ተሳትፎና በባለድርሻ አካላት ቅንጅት በመጠበቅ፣ በማልማት፣ በማስተዋወቅና የአገራችን መልካም ገጽታ በመገንባት ዘላቂና ተወዳዳሪ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ መፍጠር እና የላቀ ማህበራዊ፣ ምጣኔ ሃብታዊና ስነ-ምህዳራዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ።

### ራዕይ

በ2022 የቱሪዝም ዘርፍን በማላቅ ከቀዳሚ የአገር ብልፅግና መሠረቶች አንዱ ማድረግ።

### እሴቶች

- ብዝሀነትን ማክበር
- እንግዳ ተቀባይነት
- ግልጸነት
- ተጠያቂነት
- ለውጥ ዝግጁነት
- የላቀ አገልግሎት
- አሳታፊነት

## 2. በ2017 በጀት ዓመት በአፈፃፀም ሂደት የታዩ መልካም ተሞክሮዎች፣ ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

### 2.1 ያጋጠሙ ችግሮች

- በየጊዜው የሚፈጠሩ የፀጥታ ችግሮች በቱሪት ፍሰት እና በዱር እንስሳት በጥበቃና በቅርስ እንክብካቤ ስራዎች ላይ ተፅዕኖ ማሳረፋቸው።
- በዱር እንስሳት አጠቃቀም የህግ ክፍተቶች መኖር፤ በተለይም ከዱር እንስሳት ፊልም ቀረጻና ከዱር እንስሳት ከፍያዎች ጋር በተያያዘ
- በባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ ውስጥ 200 ሄክታር መሬት ለኢንቨስትመንት መሰጠቱና እስከአሁን ችግሩን ለመፍታት ውሳኔዎች ቢተላለፉም ተግባራዊ አለመደረጉ፤

- የህግ ተከባሪነት በጣም ዝቅተኛ መሆንና ህገወጦች ተገቢን የህግ ውሳኔ አለማግኘት
- በኦሞ ብሄራዊ ፓርክ ከደቡብ ሱዳን በመጡ ታጣቂ ሀይሎች በዱር እንስሳቱና በብሄራዊ ፓርኩ ሰራተኞች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱ
- በ2017 በጀት ዓመት ለዘርፉ የተመደበው በጀት ካለው መሰረታዊ ፍላጎት አንጻር ሲታይ አነስተኛ መሆኑ፤
- በተቋማቱ ከፍተኛ የሆነ የመስክ ተሽከርካሪ እጥረት ያለባው መሆኑ፤
- አዲስ እና ዳግም ደረጃ ምደባ የተደረገልቸው ሆቴሎች አስገዳጅ የእሳት አደጋ መስፈርት አለማሟላት፤
- በሚኒስቴሩ ውስጥ አንዳንድ የስራ ክፍሎች ማለትም መስህብ ልማት፣ ቱሪዝም ግብይትና ፕሮሞሽን፣ በማይስ ቱሪዝም እንዲሁም የቱሪስት አገልግሎቶች ብቃት ማረጋገጥና ደረጃ ምደባ ስራ ዘርፎች የሰው ሃይል እጠረት መኖሩ፤

## 2.2 የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- የሁነት ቱሪዝም ላይ ትኩረት በማድረግ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች በኢትዮጵያ እንዲካሄዱ የማድረግ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ሁኔቶችን በመፍጠር የቢዝነስ ቱሪስቶች ቁጥር እንዲጨምር ተደርጓ፡፡ የዱር እንስሳት ጥበቃ ስራዎችን በተመለከተ ያሉትን የመገናኛ እና የትራንስፖርት አማራጮች በመጠቀም በአካል በመገኘት ለጥበቃ ቦታዎች ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡
- በዱር እንስሳት አጠቃቀም ያሉትን የህግ ክፍተቶች በተመለከተ ረቂቅ የህግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት ለቱሪዝም ሚ/ር መቅረቡና በአፈጻጸሙ ላይም ክትትል እየተደረገ መሆኑ፤
- በዱር እንስሳት ስፍራዎች የሚካሄዱ ኢንቨስትመንቶችን በተመለከተ ኢንቨስተሮቹ ከመጠለያው ክልል እንዲወጡ የተላለፈው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዲደረግ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፤
- በየደረጃው ለሚገኙ የህግ አስከባሪ አካላት የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡
- በኦሞ ብ/ፓርክ ወንጀል የፈጸሙ የደቡብ ሱዳን ዜጎች ተጠርጣሪዎች በፌዴራል ፖሊስና በሀገር መከላከያ ሰራዊታችን ድጋፍ በህግ ቁጥጥር ስር ውለው ጉዳያቸው እንዲጣራ መደረጉ፤
- የተሽከርካሪ እጥረቶችን ለመቀነስ የአሰራር ማሻሻያዎችን በማድረግ የተሽከርካሪ አጠቃቀምን ውጤታማነት በማሳደግ ችግሩን ለመቀነስ ተሞክሯል፡፡ በሌላ በኩል የዱር እንስሳት ባለስልጣን ያለበትን ከፍተኛ የተሽከርካሪ ችግር በተወሰነ ደረጃ

ለመቅረፍ የአጋር ድርጅቶችን ድጋፍ እና ትብብር በመጠየቅ የልማትና ጥበቃ ሥራዎችን ለማከናወን ጥረት ተደርጓል፡፡

- ❖ ሆቴሎች አስገዳጅ የእሳት አደጋ መከላከል መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ግንዛቤ የመፍጠር እና ሙያዊ እገዛ የማድረግ ስራ ተከናውኗል፡፡
- ❖ ያለውን የሰው ሃይል አቅም በማልበትና በማነሳሳት ስራዎች ለማከናወን ጥረት ተደርጓል፤

## 2.3 በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

- ከቪዛ አሰጣጥ ጀምሮ ጎብኝዎች አገራን ገብተውና ጎብኝተው እስኪመለሱ ድረስ ባለው የቱሪዝም እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚሰጡ አገልግቶችን ጥራት ማሻሻል፣ አሰራሮችን ማዘመንና የአገልግሎት ልህቀትን ማረጋገጥ፣

- የቱሪስት አገልግሎት ደረጃ ምደባ፣ ብቃት ማረጋገጥ፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ስርዓቶችን በማጎልበት እንዲሁም የተለያዩ የአገልግሎት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በመተግበር እና ጠንካራ የቱሪስቶች ግብረ መልስ ስርዓት በመዘርጋት በሆስፒታሊቲ አገልግቶችን ጥራት ማሻሻልና የጎብኝዎችን እርካታ ማሳደግ፣

- የቱሪዝም ፈንድ አሰራር ሰርዓት በመዘርጋት እንዲሁም ከፋይናንስ ተቋማትና ከልማት አጋሮች ጋር ጠንካራ ትስስር በመፍጠር ለዘርፉ ልማት አስፈላጊ የሆነ የፋይናንስ አቅርቦት በማረጋገጥ የመዳረሻ ልማት፣ የቱሪዝም ግብይትና ብራዲንግ፣ የአገልግሎት ጥራት ማሻሻል እንዲሁም የሰው ሃይል ልማት ስራዎችን እንዲሁም ሌሎች ስትራቴጂካዊ ጉዳዮችን ማላቅ አስፈላጊ ነው፣

- ምቹ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት አሰሳሮችን በማጠናከር፣ ውጤታማ የማበረታቻ አሰጥጥ ስርዓት ተግባራዊ በማድረግ እና የኢንቨስትመንት እድሎችን በተመለከተ መረጃዎችን በጥራት ተደራሽ በማድረግ የውጭና የአገር ውስጥ ባለሃብቶችን ቁጥር ማሳደግ እና የግል ዘርፉን ሚና የበለጠ ማጎልበት ያስፈልጋል፣

- በመንግስትና በግል ዘርፉ መካከል እንዲሁም አጠቃላይ በቱሪዝም ተዋንያን መካከል አምዳዊና የጎንዮሽ ትስስሮችን በማጠናከርና የማፈፃም አቅምን በማሳደግ የቱሪዝም ልማት አንኳር ማነቆዎችን እንዲቀረፉ በማድረግ የዘርፉን ልማት ማፋጠን፣

- አስተማማኝ የቱሪስቶች ደህንነት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግና ጎብኝዎች ከሚደርስባቸው ጉዳት እንዲሁም ከሚፈጠርባቸው ስጋት ነፃ ማድረግ ያስፈልጋል፣

ፀጥታና ደህንነትን በማረጋገጥ የቅርሶችና የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ስራዎችን ማጠናከር፣

- በነባር የቱሪስት አመንጭ ሀገራት የገበያ ድርሻን ለማጠናከር እንዲሁም አዳዲስ የቱሪዝም ገበያዎችን በማስፋፋ የሚያስችሉ ውጤታማ የግብይትና ፕሮሞሽን ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ በማድረግ እንዲሁም ጠንካራና የተቀናጀ የገፅታ ግንባታ ስራዎችን በማከናወን ከኮቪድ በኋላ የተፈጠረውን እምቅ የገበያ ፍላጎት በመጠቀም ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፣

- ሀገር አቀፍ የቱሪዝም ሃብቶች ልየታ (National Tourism Resource Mapping) በማካሄድ አገራችን ያላትን እምቅ የቱሪዝም ሃብቶች ዓይነት፣ መጠንና ስብጥር በጥልቀት በመለየት በተቀናጀ መንገድ (Clustering) ለማልማት የሚያስችሉ የመዳረሻ ልማት ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ቀርፆ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፣

- ለዘላቂ ቱሪዝም ልማት መረጋገጥ ወሳኝና ደጋፊ መሰረተ ልማቶች እንዲሟሉ በማድረግ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በማስፋፋትና ተወዳዳሪነታቸውን በማሳደግ ኢትዮጵያ ተመራጭ የጎብኝዎች መዳረሻ እንድትሆን ማስቻል፣ የአካባቢ ማህበረሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣

- በዘርፉ የሚስተዋሉ የሰው ሃይል አቅም ክፍተቶችን ለመሙላት እንዲሁም የሰው ሃብት ፍላጎትና አቅርቦትን ለማጣጣም የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች፣ አሰራር ስርዓቶችና የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፣

- የኢትዮጵያን ጥበቃ ቦታዎችን ሽፋን ማሳደግ፤ አሁን ያሉትንም ጥበቃ ቦታዎች የመረጃ ቋት ማደራጀት፤

- የግሉ ዘርፍ፣ ማህበረሰቡ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር እንዲሳተፉ ማበረታታት፤

- የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎቹ ካለባቸው ከፍተኛ ሰው ሰራሽ ጫና ማላቀቅ የሚያስችል አሳታፊና የተቀናጀ የጥበቃና ቁጥጥር ሥርዓት በማጠናከርና በማዘመን የብሔራዊ ፓርኮችና መጠለያዎችን ህልውና ከጥፋት መታደግ፣

- የተጎሳቀሉ የጥበቃ ቦታዎች ሥነ-ምህዳሮች መልሶ እንዲያገግሙ የተቀናጀ የሥነምህዳር ጥበቃና ልማት ስልት /Integerated Landscape Conservation and Development Approach/ ገብራዊነትን ማበረታታት፤ እንዲሁም የሥርዓት

ምህዳር ውክልናቸው እንዲሰፋ ማድረግ እና ቁልፍ አገናኝ /connectivity/ የሆኑ የዱር እንስሳት መኖሪያ ቦታዎች በአሳታፊነት መጠበቅ፤

- በተለያዩ ጫናዎች ቁጥራቸው የተመናመኑና ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎች እንዲያገግሙና ቁጥራቸው እንዲጨምር ደጋፊ የሆኑ የጥበቃ ስልቶችን /semi-insitu captive breeding programme/ መንደፍና መተግበር፤
- በዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢያቸው የሚደርሱ አደጋዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ስትራቴጂ መንደፍና መተግበር፣
- ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣውን በሰውና በዱር እንስሳት መካከል የሚከሰት ግጭትን ለመከላከልና የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ የተዘጋጀውን ስትራቴጂ ለመተግበር የሚያስችል ተቋማዊ አቅም መፍጠር፣
- የሀገሪቱን ቅርሶች ምዝገባ ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ ሊያሳድግ የሚችል የቅርስ ምዝገባ ስትራቴጂ መንደፍ፣
- በቅርስ ጥገናና እንክብካቤ የግሉ ዘርፍ ይበልጥ ተሳታፊ የሚሆንበትን ስትራቴጂ ማዘጋጀት፡
- በቅርስ ምዝገባ ጥበቃና እንክብካቤ ስራዎች ከክልሎች እና እስከታች ባሉ መዋቅሮች ጋር የተናበበ እና ግልፅ የሃላፊነት ክፍል የሚያሳይ አሰራር መዘርጋት፡
- በቅርስ አመዘጋገብና ጥናት ማንዋሎችና መመሪዎችን ለክልሎችና ለባለድርሻ አካላት በተከታታይ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች በመስጠት ስራዉ በባለቤትነት እንዲመራ ማድረግ፡፡

## 3. የእቅዱ ታሳቢዎች

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይህንን ዓመታዊ የዘርፍ ልማት እቅድ ሲያዘጋጅ ልዩ ልዩ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎችን ታሳቢ አድርጓል፡፡ እቅዱ በዋናነት መነሻ ያደረገው የ10 ዓመት የረጅም ጊዜ እቅድ እና የመካከለኛ ዘመን እቅድን ሲሆን የተቃኘውም የ10 ዓመት እቀዱን በተሻለ ፍጥነትና ውጤታማነት ለማሳካት በሚያስችል መልኩ ተመንዝሮ የተዘጋጀ ነው፡፡ በመሆኑም ባለፉት የእቅድ ዘመናትን የአፈፃፀም ሂደት በጥልቀት በመገምገም የተገኙ መልካም ውጤቶችን፣ የአፈፃፀም ክፍተቶች እና ያጋጠሙ ችግሮችን እንዲሁም ዘርፉን ተብትበው አስረው በሚፈለገው ፍጥነት እንዳያድግ ያደረጉ ቁልፍ ተግዳሮቶች መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡ የክልልና ባለድርሻ አካላት ጥያቄዎች እና ፍላጎቶች የእቅዱን

ታሳቢዎች ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የሌሎች ሀገራትን የቱሪዝም ልማት ተሞክሮዎችና መልካም ልምዶችን በመዳሰስ ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥመው የሚሄዱበትን አኳኋኗን ታሳቢ አድርጓል፡፡

የቱሪዝም ግብይትና ፕሮሞሽን ስራዎችን በተመለከተ እቅዱ ሲታቀድ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎችን ታሳቢ ያረገ ሲሆን በዋነኛነት ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ በኂላ በአለም ላይ ያለው የቱሪዝም እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍጥነት እያንሰራራ መምጣቱን እና ይህ ሁኔታ የበለጠ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በአልም ብሎም የአፈሪካ የቱሪዝም እድገት አብሮ እያደገ መምጣትን ተከትሎ በአገራችንም የሚታየው የቱሪዝም እንቅስቃሴ የገጠሙትን የተለያዩ መሰናክሎችና ማነቆዎች ተቋቁሞ መልካም መሻሻሎችን እያሳየ ያለ መሆኑ ከግንዛቤ ገብቷል፡፡

ኢትዮጵያ ከኮቪድ ወረርሽኝ በኂላ በፍጥነት ካገገሙ የቱሪስት መዳረሻዎች ውስጥ ከአፍሪካ ቀዳሚ መሆኗን የአገራችን ቱሪዝም ለማሳደግ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር መሆኑን መሰረት ያደረገ ነው፡፡

ዓለም አቀፉ የቱሪዝም እንቅስቃሴ በአሁኑ ወቅት ከከቪድ በፊት ወደ ነበረበት ደረጃ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ አገግሟል፡፡ የሀገራችን ቱሪዝም እንቅስቃሴም በወረርሽኙና በጦርነት ምክንያት ተፈጥሮበት ከነበረው ጫና ተላቆ አበረታች መሻሻሎችን ከማሳየት ዓልፎ ባፈው በጀት ዓመት ከፍተኛ ውጤት አስመዝግቧል፡፡ የዓለም ቱሪዝም ገበያ ፍላጎት እየተለወጠ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የጎብኝወች ወደ ሃገራችን የመጎብኘት ፍላጎትም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣት ወደ አፍሪካ ብሎም ኢትዮጵያ እንዲሁም ከዚህ በፊት የቱሪዘም እንቅስቃሴ ወዳልነበረባቸው ቦታዎች መጓዝ እየተለመደ መጥቷል፡፡

የአፍሪካ ሀገራትን እርስ በእርስ ይበልጥ የሚያስተሳስሩ ምቹ ቀጠናዊ አሰራሮችን ለምሳሌ የቪዛና የጉምሩክ ሂደቶች እና የህግ ማዕቀፎች ማሻሻያዎች እንደሚኖሩ በተለይም የአፍሪካ ነፃ የንገድ ቀጠና እውን ለማድረግ የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓቶች እየተዘረጉ መሆኑ ለቱሪዝም እድገት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ህ ሁኔታ የቱሪዝም ንግድ ትስስሮችን በመፍጠር፣ የተቀናጀ መሰረተ ልማትና የቱሪዝም ምርት ልማት ስራዎችን በማጎልበት፣ ትብብራዊ የፕሞሽንና ብራንዲንግ ስራዎችን በማጠናከር እንዲሁም ቀላልና የተሳተለ የጎብኝዎችን እንቅስቃሴ በማረጋገጥ እንዲሁም በዱር እንስሳት እና ቅርስ ጥበቃ ስራዎች ቅንጅትን በማጠናከር ረገድ ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

በሀገራችን ተፈጥሮ የነበረው የእርስ በእርስ ጦርነት በቱሪስት መስህቦች፣ በቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት፣ በመዳረሻ አካባቢ ማህበረሰቦች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ከማሳደሩም በዘለለ ከጦርነቱ ጋር በተያያየዘ በውጭ መንግስታት በተሰራው የሚዲያ ዘመቻ የሀገራችን ገፅታ እንዲጠለሽ ሆኗል፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ጦርነቱ በሰላም ድርድር የታሰረ በመሆኑ የጉዞ ክልከላዎች፣ አሉታዊ የጉዞ ምክሮችና የሚዲያ አሉታዊ መረጃዎች ስርጭት በእጅጉ የቀነሰ ስለሆነ ገፅታችን በዓለም መድረክ እየተሸሻለ እንደሚመጣ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ እስከ አሁን አለም ስለ አገራችን ያለው እይታ ለመቀየር ልዩ ልዩ ተግባራትን ተነድፈው እየተሰሩ ሲሆን ከሚሲዮኖች ጋር በመተባበር የገፅታ ማሻሻያ ስራዎችን በማካሄድና በውጭ ሀገር በተለያዩ አለም አቀፍ ትሬድ ፌርና የጉዞ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በማቀናጀት የቱሪዝም ሃብቶችን የማስተዋወቅ ስራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በቀጣይም ይህ ተግባር ተጠናክሮ በስፋት የሚከናወን ይሆናል፡፡

የአገር ውስጥ ቱሪዝም እንቅስቃሴ ለዘላቂ የቱሪዝም እደገት አይነተኛ መፍትሄ እንደሆነ የታመናል፡፡ ለምሳሌ በቻይና ሃገር የአገር ውስጥ ቱሪዝም በከፈተኛ እንቅስቃሴ እንዳለው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በሃገራችንም ከዚህ በፊት የነበርው የመጎብኘት ባህልና የሚካደው የቱሪዝም እንቅስቃሴ እዚህ ግባ የሚባል ባይሆንም በአሁኑ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሰጠው ትኩረትና እያቆጠቆጠ ያለው የአገር ውስጥ ጉብኝት እንቅስቃሴ (ከሃይማታዊ ጉዞዎች በተለየ ለመዝናናት) መልካም አጋጣሚ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

መንግስት ከቅረብ ጊዜ ወዲህ ለቱሪዝም ሴክተሩ የሰጠው ትኩረት ይበል የሚያሰኝ ሲሆን የቱሪዝም ዘርፉን ክልሎችን፣ የግል ዘርፉንና ሌሎሎች ባለድርሻ አካላትን አስተባብሮ የቱሪዝም ዘርፉን የሚመራ ስራሱን የቻለ አስፈፃሚ ተቋም (ቱሪዝም ሚኒስቴር) ከማቋቋም ጀምሮ የተለያዩ የቱሪዝም መዳረሻዎችና ፋሲሊቲዎችን በማልማት አሳይቷል፡፡ በአሁኑ ወቅትም የተለያየ ስራዎች እየተሰሩና ለወደፊትም ታቅደው እንቅስቃሴ ላይ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም መንግስት እየወሰደ ያው የኢኮኖሚ ማሻሻያ እርምጃዎች በተለይም የፋይናንስ ዘርፉን እና የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፉን ለአለም አቀፍ ንግድ እየከፈተ መሆኑ ለቱሪዝም እድገት አወንታዊ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡

የቱሪዝም ልማትን ከመንግስት በሚመደብ ውስን በጀት በተሟላ መልኩ ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ያለፉት በርካታ ዓመታት ልምድ የሚያሳየው ይህን እውነት ነው፡፡ ስለሆነም ያንን እምቅ የቱሪሪም ሃብቶች መሰረተ ልማትና የቱሪሪም ፋሲሊቲዎች ተሟቶላቸው ተወዳዳሪ መዳረሻዎች ለማድረግ ከፍተኛ የሆነ የሃብት እጥረት የሚስተዋል ቢሆንም ይህ እቅድ ሲዘጋጅ የቱሪዝም ልማት ፈንድ በማቋቋም የሃብት እጥረቱን ለመቀነስ የሚያስች

የገንዘብ አቅም እንደሚፈጠር ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ለዘርፉ ከተሰጠው ትኩረት ጋር ተያይዞ የዓለም ባንክን ጨምሮ የተለያዩ Bilateral and Multi-lateral ተቋማት ዘርፉን ለገንዘብ ለማገዝ ፍላጎት ማሳየታቸው ጥሩ አጋጣሚ እንደሚፈጥር ይታመናል፡፡ ከዚህ አንፃር ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የገንዘብ አማራጮችን ለማስፋት የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ ተጨማሪ ሀብት የማፈላለግ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

የፕሮሞሽንና ገበያ ልማት፣ የመዳሻና ምርት ልማት፣ አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል፣ የዱር እንስሳት እና ቅርስ ጥበቃና ልማት ስራዎችን ለማከናወን ከዘርፎቹ ፍላጎት አኳያ በመንግስት በኩል የአቅም ውሱንነት እንደሚኖርበት የሚገመት ቢሆንም ስራዎችን ለመፈፀም የሚያስችሉ ተጨማሪ ሃብቶች በተለያዩ መንገዶች እንደሚመነጩ ተሳቢ ተደርጓል፡፡

ተቋማዊ አቅምን ከማጠናከር አኳያ እቅዱ ታሳቢ ያረገው ቱሪዝም ሚኒስቴር በአዲሱ መዋቅር መሰረት ሰራተኞች ድልድል አድርጎ ወደ ስራ የገባ መሆኑን መነደሻ በማድረግ በቀጣይ የሰው ሃይል አቅምን የማጎልበት፣ አሰራሮችን የማጠናከር  እንዲሁም ከክልችና ባለድርሻ አካላት ጋር ትስስሮች የማጠናር ስራዎችን በማከናወን የማስፈፀም አቅምን የሚያደግ መሆኑን ነው፡፡ በሂደት ላይ ያ የህግ ማዕቀፎች፣ በረቂቅ ላይ ያሉ ስትራቴጂዎችና የአሰራር ስርዓቶች በማጠናቀቅ እንዲሁም የዘርፉ ልማት አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ ስትራጂዎች፣ የአሰራር ስርዓቶችን የህግ ማዕቀፎችን ተነድፈው ተግባራዊ እንደሚሆኑ ይጠበቃል፡፡

በተመሳሳይ የዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣንና የቅርስ ባለስልጣን መ/ቤቶች የተቀረፁትን አዳዲስ መዋቅሮች መሰረት ውጤታማ የሰው ሃይል ድልድል አድርገው ወደ ስራ የሚገባ በመሆኑ አሁን ካለው አፈጻጸም በተሻለ መልኩ ለማከናወን በተለይ በጥናትና ምርምር ዘርፍ ስራዎችን ለማጠናከር ታሳቢ ከተደረጉ መካከል በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉት ናቸው፡፡ ይህም ዘርፉ የሚጠይቀዉን የሰው ኃይል፣ ግብዓት እንዲሁም አደረጃጀት ለማከናወን እንዲሁም የአሰራር ሂደቶችን ተጠያቂነትን ለማስፈን ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ የቅርስ ጥናትና ምርምር ስራ ለመስራት ወደ ሀገራችን የሚመጡ የውጭ ተመራማሪዎች መምጣት መጀመራቸውም ተስፋ ሰጪ ነው፡፡

በአለም አቀፍ ደረጃ ሙዚየምን የተመለከቱ እውቀቶች፣ ሀሳቦች፣ የግንኙነት መደላደሎች መኖራቸው እንዲሁም በሀገራችን በቅርብ አመታት ውስጥ  በፌዴራል መንግስት፣ በሀይማኖት ተቋማት፣ በዩኒቨርስቲዎችና በግለሰቦች ጭምር ሙዚየሞችን ለማደራጀት

የተስተዋሉ እና እየታዩ ያሉ እንቅስቃሴዎች፣ የአስተሳሰብ ለውጦች፣ ሰዎች ባህላቸውንና ታሪካቸውን ለማወቅ ሙዚየሞችን መዳረሻ እያደረጉ መሆኑ ደረጃ በደረጃ እየተስተዋለ መሆኑ፣ በአዲሱ ስርአተ ትምህርት ቲዎሪን በተግባር ለመደገፍ የተያዘው የፖሊሲ አቅጣጫ ውጪያዊ እና አካባቢያዊ ምቹ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱ በጎ ታሳቢዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የመካከለኛ ዘመን እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲሁም ዓመታዊ እቅዱን ለመተግበር የተለያዩ ተግዳቶች እንደሚገጥሙ እሙን ነው፡፡ የመጀመሪያው ጉዳይ የቱሪዝም ዘርፍ ከመሰረቱ የፀጥትና ደህንነት ሁኔታ መረጋገጥን የሚጠይቅ በመሆኑ ምንም አንኳን በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ተፈትሮ የነበረው ጦርነት በሰላም ስምምነት መቋጨቱ መልካም ቢሆንም አሁንም ቢሆን በአገራችን የተለያዩ አካባቢዎች የሚከሰቱ ግጭቶችና አለመረጋጋቶች የሚቀጥሉ ከሆነ በቱሪዝም እንቅስቃሴ፣ በፌዱር እንስሳት ጥበቃ እንዲሁም በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ስራዎች እንቅፋት ይፈጥራል፡
፡

በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ስራዎች የባለሙያዎች እጥረት የሚስተዋል በመሆኑ ያሉትን ባለሙያዎች በማብቃት ስራዎችን በተሸለ ጥራት መስራት የሚቻልበት እንዲሁም ተጨማሪ ባለሙያች የሚሟሉበት ሁኔታ መፈጠር እንዳለበት ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በቅርሶች ጥበቃና እንክብካቤ አኳያ ባለሙያዎችንና ሌሎች በዘርፉ የተሰማሩ ተቋራጮች እና የአማካር ድርጅቶች፣ እንዲሁም ባለድርሻ አካላት አቅም ተጠቅሞ እቅዱን በተያዘው ግዜ እና ጥራት ማስፈፀም ይጠበቃል፡፡ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ትስስሮችን በማጠናከር በእውቀት፣ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ በሰው ሀይል አቅም ግንባታ ድጋፎችን በማግኘት የመፈፀም አቅምን ማጠናከር ይቻላል፡፡

አገራችን ሰፊ ተፈጥሯዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ የቱሪዝም ሃብቶች ያላት እንደመሆኑ እነዚህን ሃብቶች መጠበቅ፣ መንከባከብ፣ ማልማትና ማስተዋወቅ ከፍተኛ ሃብት የሚጠይቅ ነው፡፡ እቅዱን በተሟላ መልኩ እውን ለማድረግ የተነደፉ ፕሮግራሞች፣ ንዑስ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በተገቢው መልኩ ፋይናንስ ማድረግ የሚያስፈልግ በመሆኑ ከዚህ አንፃር የሚመነጩ ተግዳሮቶች እንደሚገጥሙ ይጠበቃል፡፡ እስካን በነበረው ልምድ ዘርፉ ከሚያመነጨው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎችና ማበራዊ ፋይዳዎች አኳያ የሚመደብለት በጀት ተመጣጣኝነት ይጎድለዋል፡፡

## 4. የትኩረት መስኮች፣ ስትራቴጅካዊ አቅጣጫዎችና ግቦች

### 4.1 የትኩረት መስኮች

**የትኩረት መስክ 1፡ የተፈጥሮና ባህላዊ ሃብቶች ጥበቃና አጠቃቀም**

**የትኩረት መስክ 2፡ የቱሪዝም መዳረሻና ምርት ልማት**

**የትኩረት መስክ 3፡ የቱሪዘም ገበያ ልማት**

**የትኩረት መስክ 4፡ የቱሪስት አገልግሎቶች ልህቀት**

**የትኩረት መስክ 5፡ ተቋማዊ አቅም ግንባታ**

### 4.2 የ2017 ስትራቴጅካዊ ግቦች

1. ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት
2. የሀገሪቱን የቱሪዝም አለኝታዎች በመለየት መዳረሻዎችን ማልማትና ማስፋፋት
3. የዘርፉን የፋይናንስ አቅም በማሳገግ ኢንቨስትመንት ማስፋፋት እና የሚፈጠሩ የስራ እድሎችን ማሳደግ
4. የአለም አቀፍ ፕሮሞሽንና ግብይት ስራዎችን በማጎልበት የጎብኚዎች ፍሰትና የውጪ ምንዛሬ ገቢን ማሳደግ
5. የአገር ውስጥ ቱሪዝምን በማሳደግ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ
6. በቱሪዝም ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻልና ልህቀትን ማረጋገጥ
7. የዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢዎችን ጥበቃ ስራዎችን ማጎልበት
8. የቅርሶች ጥበቃ፣ እንክብካቤና ልማት ሥራዎችን ማሳደግ

### 4.3 ዋና ዋና ተግባራትና የሚጠበቁ ቁልፍ ውጤቶች

1. **ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት**

**ዋና ተግባር 1፡** የዕቅድ ዝግጅት፣ የክትትልና ግምገማ አሰራር ማሻሻል

**ዋና ተግባር 2፡** የቱሪዝም ስታቲስቲክስ ስርዓትን እና መረጃ አአስተዳደር አሰራርን ማሻሻል

**ዋና ተግባር** 3፡ የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል

**ዋና ተግባር** 4፡ የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል

**ዋና ተግባር** 5፡ የኦዲት ስራዎችን ውጤታማነት ማሻሻል

**ዋና ተግባር** 6፡ የለውጥ ስራዎችን በማጠናከርና ተቋማዊ አቅምን ማሳደግ

**ዋና ተግባር** 7፡ የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት አሰራርን ውጤታማነትን ማሻሻል

**ዋና ተግባር** 8፡ ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል ማሻሻል

**ዋና ተግባር** 9፡ የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና የክትትል ሥራዎችን ማሻሻል

**ዋና ተግባር** 8፡ የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎችን ማሻሻል

**ዋና ተግባር** 10፡ የሴቶችና ማሕበራዊ ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ማሻሻል

## 2. የሀገሪቱን የቱሪዝም አለኝታዎች በመለየት መዳረሻዎችን ማልማትና ማስፋፋት

**ዋና ተግባር** 1፡ የቱሪዝም አለኝታዎች መለየት፣ አዳዲስ መዳረሻዎችን ማልማትና ማስፋፋት

**የሚጠበቅ ውጤት፡** ደረጃቸውን የጠበቁ፣ ተመራጭና ተወዳዳሪ የቱሪዝም መዳረሻዎች

በሀገሪቱ የሚገኙ ከዚህ በፊት በአግባቡ ተለይተው ለቱሪዝም ገበያ ያልዋሉ የቱሪዝም እድሎች በጥናት የመለየት፣ በአዋጭነታቸው የተለዩ ሀብቶችን ደረጃ በደረጃ መልማት የሚችሉበትን ስርዓት በመዘርጋት እንዲለሙ ለማድረግ ይህ ዋና ተግባር ተቀምጧል፡፡

**ዝርዝር ተግባራት፡**

- በቱሪዝም መዳረሻዎች ልማት እንዲሁም በሴክተሩ በሚቀርቡና በፍልጎት ዳሰሳ ጥናት በሚለዩ ጭብጦች ማለትም በኢንተርፕራዝ ልማት እና ማህበረሰብ ተጠቃሚነት፤ በቱሪዝም መዳረሻዎች መሰረተ ልማት እና ፋሲሊቲ አቅርቦት፤በሁለንተናዊ ቱሪዝም ልማት ዙሪያ ፕሮጀክቶች በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ፤
- ተግባራዊ የሚደረጉ ነባርና አዳዲስ የመዳረሻ ልማት ፕሮጀክቶች አፈፃፀማቸውን መቆጣጠር፣ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- ቀድሞ በተዘጋጀው ሀገር አቀፍ የቱሪዝም መዳረሻዎች ስታንዳርድ መሰረት መስፈርቶቹን ያሟሉ መዳረሻዎችን በመምረጥ ማዘጋጀት፤
- ሀገር አቀፍ የቱሪዝም ሃብቶች ልየታና ትንተና ስራ (Tourism Resource Mapping) ማከናወን፤(በውጭ ድጋፍ)

- እንቅስቃሴን መሰረት ያደረጉ ማለትም የሃይኪን፣ ትሬኪንግ፣ ፓራግላይዲንግ፣ የውሃ ላይ ተግባራት፣ ባሉኒንግና…ወዘተ የቱሪዝም ዘርፍን ለማስፋፋት በተመረጡ ቦታዎች ኹነቶችን ማዘጋጀት፤
- ልዩ የቱሪስት ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ የቱሪዝም ውጤት አይነቶችን (special interest tourism products) በጥናት በመለየትና በፕሮጀክት ደረጃ በመቅረፅ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ማልማት፡፡ *የጤና ቱሪዝም፣ የእርሻ ቱሪዝም፣ የተራራ ቱሪዝም፣ የቡና ቱሪዝም…ወዘተ፡፡*
- ከፕሮጀክት ዝግጅት ተግባር ጋር በቅንጅት የሚከናወን የቱሪዝም መሰረተ ልማትና ፋሲሊቲዎች ግንባታን ለማከናወን የሚያስችሉ ጥናቶችን ማካሄድ፤
- ከፕሮጀክት ዝግጅት ተግባር ጋር በቅንጅት የሚዘጋጅ አዳዲስ የቱሪዝም ምርቶችን በጥናት በመለየት ለልማት ዝግጁ ማድረግ፤

**ዋና ተግባር 2፡** በሀገሪቱ ነባር መዳረሻዎች ላይ እሴት በመጨመር ተወዳዳሪነታቸውን ማሳደግ

**የሚጠበቅ ውጤት፡** *ያደገ የቱሪዝም መዳረሻዎች ተወዳዳሪነት*

ይህ ዋና ተግባር የቱሪዝም መዳረሻ ስፍራዎችን የተወዳዳሪነት ደረጃቸው እንዲሻሻል ለማድረግ እሴት የሚጎድላቸውን በመለየት ይህንኑ ክፍተት የመሙላት ስራ በማከናወን የመዳረሻዎችና መስህቦችን አቅም መሻሻል ስራን ይመለከታል፡፡

**ዝርዝር ተግባራት፡**

- በተመረጡ ክልሎች/መዳረሻዎች ነባር የቱሪስት መረጃ ማዕከላትን ለማጠናከር የሚያስችሉ ድጋፎችን ማከናወን፤
- የዓለም ምርጥ የቱሪዝም አሸናፊ መንደሮች፣ በተመረጡ ማህበረሰብ አቀፍ መዳረሻዎች፣ በቱሪዝም መዳረሻ ልማት ስራ ጥሩ ተሞክሮ ያላቸውን በመለየት ለሌሎች ልምድ እንዲያካፍሉ ማድረግ፤
- በክልሎች እና በግል መዳረሻ አስተዳደር አካላት ተግባራዊ የሚደረጉ በተመረጡ የቱሪዝም መዳረሻዎች የቱሪስት ፋሲሊቲ ግንባታዎች እንዲመሰረቱ ለማስቻል ተከታታይ ድጋፎችን ማከናወን፤
- በሌሎች ተቋማት ተግባራዊ የሚደረጉ የመሰረተ ልማት የማሻሻያ ስራዎች በመከታተል በጋራ ማስፈፀም፡፡

**ዋና ተግባር 3፡** የቱሪዝም መሰረተ ልማትን ማስፋፋት

**የሚጠበቅ ውጤት፡** *ያደገ የቱሪዝም መሰረተ ልማት የተሟላላቸው የቱሪስት መስህቦች*

ይህ ዋና ተግባር በመዳረሻዎችና መስህቦች አካባቢ የሚገኙ የኀብኚውን ተጨማሪ የቱሪዝም ምርት አቅርቦትና የግብይት ፍላጎቶች ለማማላት የሚረዱ የቱሪስት ምርት አይነቶችን በጥናት የመለየት፣ አይነትና የጥራት ደረጃቸው እንዲሻሻል የሚረዱ ተግባራትን በመፈፀም የኀብኚን የቆይታ ጊዜ የማራዘም፣ የግብይት እድሎች የመጨመር፣ ለአካባቢው ማህበረስብ ተጠቃሚነትና የተሳትፎ እድሎችን ለመጨመር የሚረዱ አማራጮችን ማሳደግን ይመለከታል፡፡

**ዝርዝር ተግባራት፡**

- ከጎረቤት ሀገራት ጋር ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል ቀጠናዊ የቱሪዝም ምርት ልማት አሰራር መዘርጋት፤
- በተለያዩ መዳረሻዎች (በብሔራዊ ፓርኮች፣ ዓለም አቀፍ ቅርሶች፣ ትልልቅ የመዳረሻ ልማት ቦታዎች…) የቱሪስት ምርቶችን ለማልማት የሚስያችሉ እድሎችን በጥናት መለየት፤
- በተመረጡ ቦታዎች (በብሔራዊ ፓርኮች፣ ዓለም አቀፍ ቅርሶች፣ ትልልቅ የመዳረሻ ልማት ቦታዎች…) ምርቶችን ለመቅረፅ፣ ለማልማት፣ ለማስተዋወቅና ለገበያ ተደራሽ ለማድረግ የሚያችል ፓኬጅ ማዘጋጀት፣ በትብብር ተፈፃሚ ማድረግ፤
- ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የቱሪዝም ገፀ-በረከት ምርቶች ማምረቻና ማሳያ ማዕከላት ማቋቋም፤
- በክልሎች/መዳረሻዎች የሚገኙ የቱሪዝም ምርቶችን ጥራት ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመቆጣጠር የሚያችሉ ስታንዳርዶችና አሰራሮች ማዘጋጀት፣ ተግባራዊ ማድረግ፣

**ዋና ተግባር** 4፡ የቱሪስት ምርቶችን ዓይነትና ደረጃ ማሳደግ

የሚጠበቅ ውጤት፡ *ያደገ የቱሪስት ምርቶች ዓይነትና የጥራት ደረጃ*

## 3. የዘርፉን የፋይናንስ አቅም በማሳገግ ኢንቨስትመንት ማስፋፋት እና የሚፈጠሩ የስራ እድሎችን ማሳደግ

**ዋና ተግባር** 1፡ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋትና ማሳደግ

**የሚጠበቅ ውጤት፡** *ያደገ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት*

**ዋና ተግባር** 2፡ የዘርፉን የፋይናንስ አቅም ማጎልበት

**የሚጠበቅ ውጤት፡**

- የተሸሻለ የፋይናንስ ምንጮች
- የተሸሻለ የፋይናንስ አቅርቦትና የፋይናንስ አጠቃቀም ውጤታማነት

ይህ ዋና ተግባር የቱሪዝም መስህብ ልማት ስራዎችን የተሳካ ለማድረግ የሚረዱ የኢንቨስትመንት እድሎችን መለየት፣ የልማት ክፍተት በሚታይባቸው አካባቢዎች ተሳትፎ እንዲደረግ የኢንቨስትመንት ሁኔታዎችን እና መደላድሎችን በማመቻቸት የቱሪዝም ዘርፉን እድገት መደገፍን ያካትታል፡፡

**ዝርዝር ተግባራት፡**

- በተመረጡ የቱሪስት መዳረሻዎች ማለትም በብሔራዊ ፓርኮች፣ በአለም አቀፍ ቅርሶች፣ በትልልቅ መዳረሻ ልማት ፕሮጀክቶች (በገታ ለሀገርና ገበታ ለትውልድ)፣ በአለም ምርጥ የቱሪዝም መንደሮችና ወዘተ ላይ በሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ኢንቨስት እንዲያደርጉ የኢንቨስትመንት እና የትዉዉቅ ጉዞዎች ማዘጋጀት፤
- ዓመታዊ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ፎረም ማካሄድ፤
- የቱሪዝም መዳረሻ ልማት ስራዎችን ለማስፋፋት የሚያስችሉ ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ማዘጋጀት፡፡ (በቱሪዝም ኢንቨስትመንት፣ በአስጎብኚነት፣ በመዳረሻ አስተዳደር፣ በመዳረሻ ልማት….)፡፡
- በመንግስት፣ በግል ባለሃብቶችና በአካባቢ ማህበረሰብ (PPP) ሽርክና የቱሪዝም ሀብቶችና መዳረሻዎችን ለማልማት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፤
- አለም አቀፍ መድረኮችና የሀገር ውስጥ መድረኮችን በመጠቀም የውጭ እና የአገር ዉስጥ የቱሪዝም ኢንቨስትመንቶች (በሎጅ፣ በሆቴል፣ በሬስቶራንትና ወዘተ) ባለሀብቶች እንዲሰማሩ ለማስቻል የተቀናጁ ድጋፎች ማድረግ፤
- ለዘርፉ ልማት ማነቆ የሆኑ አሰራሮችንና የህግ ማዕቀፎችን ማለትም የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ ማበረታቻዎች ይዘትና መጠን፣ የህግ ማእቀፎች፣ የሴክተሮች ትብበር ስርዓትን ለማሻሻልና ወዘተ በጥናት መፈተሽና እንዲሻሻሉ ማድረግ፤
- የሀገር ውስጥ የማስታወቅያ ዘዴዎችንና በይነ መረብን በመጠቀም በቼይን ሆቴል ምስረታ የሚሰማሩ ባለሃብቶችን በቀጥተኛ የውጪ ኢንቨስትመንት (FDI) እንዲገቡ እና ኢንቨስት ኢንዲያደርጉ ማስቻል፣ ተከታታይ ድጋፎችን መስጠት፤
- የፍላጎት ጥናቶችን መሰረት ያደረገ ከግል ባለሃብቱ ጋር በመቀናጀት በተፈጥሮ ሀብትና ፓርኮች አካባቢ የመዳረሻ ልማት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ቀረፃ ማከናዎን፤
- ጥናቶችን መሰረት ያደረገ የቱሪዝም ሀብቶች ስብጥር መሰረት በማድረግ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ቀጠና (clusters) መፍጠር፤

- ቀድሞ የተዘጋጀ የቱሪዝም መዳረሻ ኢንቨስትመንት ሰነድ (Hand Book) ተደራሽ ማድረግና ማሰራጨት፤

**ዋና ተግባር 2፡** በዘርፉ የሚፈጠሩ የስራ እድሎችን ማሳደግ

**የሚጠበቅ ውጤት፡** በቱሪዝም ዘርፍ የሚፈጠሩ የስራ እድሎችና የዜጎች ተጠቃሚነት

በዘርፉ የሚፈጠሩ የስራ እድሎችን ለማሳደግ የሚረዱ ስልቶችን በመደገፍና በማስፈፀም በቱሪዝም መዳረሻዎች አካባቢ የሚገኙ የማህበረሰብ ተጠቃሚነት ማሳደግን ያካትታል፡፡

**ዝርዝር ተግባራት፡**

- በሀገሪቱ በሚገኙ ባህላዊ፣ ተፈጥሯዊና ታሪካዊ የመስህብ ሀብቶች ዙሪያ የሚገኙ የስራ ዕድሎች በጥናት መለየት፣ ዕድሎችን ማሳየት፤
- በተመረጡ ክልሎች/መዳረሻዎች የቱሪዝም ኢንተርፕራይዞችን መመስረት፣ ተከታታይ ድጋፍ ማድረግ፤
- የቱሪዝም ኢንተርፕራይዝ ልማት የአሰራር ማዕቀፍ መንደፍ፤
- በቱሪዝም ዘርፍ ለሚሰለጥኑ ሰልጣኞች ዓመታዊ የስራ ዕድል ትስስር ጆብ ፌር ፕሮግራም ማዘጋጀት፤
- ለቱሪዝም ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የተቀናጀ ድጋፍ ማድረግ፤
- በተመረጡ ክልሎች/መዳረሻዎች በማህበረሰብ ተኮርና በኢኮቱሪዝም ልማት የመዳረሻ አካባቢ ማህበረሰቦች ተጠቃሚ የሚሆኑባቸውን ፕሮጀክቶች መቅረፅ፤

## 4. የአለም አቀፍ ፕሮሞሽንና ግብይት ስራዎችን በማጎልበት የጎብኚዎች ፍሰትና የውጪ ምንዛሬ ገቢን ማሳደግ

**ዋና ተግባር 1፡** ውጤታማ አለም አቀፍ ፕሮሞሽን ስራዎችን በማጎልበት የውጪ ሀገር ጎብኚ ፍሰትን እና የገበያ ድርሻ ማሳደግ

**የሚጠበቅ ውጤት፡**

- ያደገ የውጪ ሀገር ጎብኚዎች ፍሰትን
- ያደገ የቱሪዝም ገበያ ድርሻ
- የጨመረ ከዘርፉ የተገኘ የውጭ ምንዛሪ መጠን
- የተሻሻለ የሀገር ገፅታ

**ዝርዝር ተግባራት**

- በሰባት አለም አቀፍ ንግድ ትሪኢቶች (ኒውደሊ፣ ቤርሊን፣ ሻነጋይ፣ ብራዝል፣ ዱባይ፣ ሞስኮ እና ኮፐታዎን) ውጤታማ የቱሪዝም ፕሮሞሽን ስራዎች መስራት እና የገበያ ትስስር ማጠናከር
- የአለም አቀፍ የፕሮሞሽንና ገጽታ ግንባታ አሰራር (Directives for Participation International Trade Fairs /Exhibitions) ማዘጋጀት፣
- የሀገራችን የቱሪስት መስህቦች እና ቱሪዝም ብራንድ የሚያስተዋውቁ 7 አይነት የስጦታ እቃዎች (Giveaways) ማሰራትና ማሰራጨት፣
- በሰባት አለም አቀፍ መድረኮች ላይ በመሳተፍ የB2B መድረኮችን መፍጠር 100 የገበያ ትስስር በመፍጠር የቱሪዝም ገበያ ድርሻ ማስፋፋት፣
- በአለም አቀፍ መድረኮች ላይ ለፕሮሞሽን ስራ የሚያገለግሉ የተለየዩ ህትመቶችን ማዘጋጀት፣
- የድምጽ፣ የምስል፣ የህትመት፣ instrumental sound እና የVR በስድስት ቋንቋዎች ማለትም በእንግሊዝኛ፣ ቻይንኛ፣ ስፓኒሽ፤ ፈረንሳይኛ፤ ጃፓንኛ እና ጀርመንኛ ቋንቋ በማዘጋጀት በአለም አቀፍ የቱሪዝም ግብይት መድረኮች፣ በቱሪስት መረጃ ማዕከላት፣ በውጪ ሀገር ኢምባሲዎች ላይ ማሰራጨት የቱሪዝም ማስተዋወቂያ ስራዎችን መስራት፡፡
- የStopover ጉብኝት አማራጮች ከኢትዮጵያ አየር መንገድ /EthioHoliday/ ጋር በመቀናጀት ማስተዋወቅ፣
- ከዲያስፖራ ኤጀንሲ ጋር በመተባበር አዳዲስ ፕሮግራሞችን መንደፍ እና የዲያስፖራ ተኮር የፕሮሞሽን ስራዎችን መስራት፣
- የሀገራችንን ገጽታ ለመገንባት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ሽፋን ባላቸው 2 ታዋቂ ሚዲያዎች ተከታታይ የሚዲያ ፕሮሞሽን ስራ መስራት፣
- የኢትዮጵያን ቀን ከኢምባሲዎች ጋር በማክበር የቱሪዝም ሀብቶችን ማስተዋወቅ፡፡

**ዋና ተግባር 2፡ የቱሪስት መረጃ ማዕከላት አገልግሎቶች ደረጃ እና የመረጃ ተደራሽት ማሻሻል**

**የሚጠበቅ ውጤት፡** *ያደገ የቱሪስት መረጃዎች ጥራትና ተደራሽነት*

**ዝርዝር ተግባራት**

- የቦሌ አለም አቀፍ ተርሚናል እና የመስቀል አደባባይ የቱሪስት መረጃ ማዕከላትን በአለም አቀፍ ስታንዳርድ መሰረት ማደራጀት፡፡
- በሀገራችን ለሚገኙ 13 የቱሪስት መረጃ ማዕከላት መረጃ ሰጪ ምልክቶችን (I-sign፣ አቅጣጫ ጠቋሚና ኦፊስ ሳይን ቦርድ) ማሰራትና መትከል

- መሰረታዊ የቱሪስት መረጃዎችን በ6 ክልሎችና ከ6 ተቋማት በማሰባሰብና ወቅታዊ በማድረግ በመረጃቋት (Data Base) ማደራጀትና ተደራሽ ማድረግ፡፡
- የቱሪስት መረጃ ማዕከላት የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃንና የመረጃ ጥራትን ለመለካት የሚያስችል ጥናት ማከናወን፡፡
- የቱሪስት መረጃ ማዕከላት የአሰራር ስርዓትና ስታንዳርድ መመሪያን ማፀደቅና ተግባራዊ ማድረግ፡፡
- ለፌዴራልና ለክልል የቱሪሰት መረጃ ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፡ :
- በክልል የሚገኙ የቱሪስት መረጃ ማዕከላት ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ

**ዋና ተግባር 3፡ ጠንካራ የዲጂታል ፕሮሞሽንና ማርኬቲንግ አሰራር በመተግበር የኦን ላየን ሽፋን ማሳደግ**

**የሚጠበቅ ውጤት፡** *ያደገ የኦንላይን ሽፋን*

**ዋና ተግባር 4፡ MICE ቱሪዝም እና ስቶፐኦቨር ቱሪዝምን ማሳደግ**

**የሚጠበቅ ውጤት፡**

- ያደገ የቢዝነስ ቱሪስቶች መጠን
- የMICE ቱሪዝም ተወዳዳሪነት
- ያደገ የስቶፐኦቨር ቱሪስቶች መጠንና የተገኘ ገቢ

## ዝርዝር ተግባራት

- የጥናት እና ምርምር እንዲሁም የቢዝነስ ልማት ተግባራትን በተለይም በሀገራችን የሚከናወኑ ኹነቶችን መረጃ የመሰብሰብ፥ በሚከናወኑ ኹነቶች የደንበኞች እርካታ መረጃን መሰብሰብ
- በእሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን የሙያ ብቃት በማረጋገጥ እና እውቅና መስጠት
- አማራጭ የማይስ ቱሪዝም ከተሞችን ማጥናት እና መደገፍ
- በኢትዮጵያ የቱሪዝም እሴት ሰንሰለቶች ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶችን ከከዓለም አቀፍ ቱሪስት አመንጪ ሀገራት እና የኹነት ዘርፍ ተዋንያን ጋር የሚያገናኝ በየዓመቱ የሚከናወን ሀገር በቀል ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ዘርፍ ንግድ ትርኢት ማዘጋጀት
- ዘርፉን አስመልክቶ የተለያዩ ጥናቶችን ማከናወን
- ኮንቬንሽን ማዕከላት እንዲገነቡ ማስቻል
- የሚከናወኑ ኹነቶችን ማስተዋወቅ፤ ኹነቶችን መደገፍ፥ ድህር እና ቅድመ ኹነት ጉብኝት ማመቻቸት

- Meeting planners guide and incentive planners guide ማዘጋጀት
- የማይስ ቱሪዝም ብራንድን ማስተዋወቅ
- የኢትዮጵያ ኮንቬንሽን ቢሮ ድረገፅን እና ማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም የዲጂታል ፕሮሞሽንና ማርኬቲንግ ተግባራትን ማከናወን
- የተለያዩ ሙያ ማህበራትን እና ድርጅቶችን በማሳተፍ ኹነቶችን በሀገራችን እንዲከናወን ማስቻል፥
- በሶስት (3) የተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ በመገኘት ማስተዋወቅን የሚያካትት ነው።

## 5. የአገር ውስጥ ቱሪዝምን በማጎልበት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅዖ ማሳደግ

**ዋና ተግባር 1፡ የጉብኝት ባህልን በማሻሻል የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ማጎልበት**

**የሚጠበቅ ውጤት፡**

- የተሸሻለ ግንዛቤና የጉብኝት ባህል
- ያደገ የአገር ውስጥ ቱሪስቶች ቁጥርና ከአገር ውስጥ ቱሪዝም የተገኘ ገቢ

**ዝርዝር ተግባራት**

- በተለያዩ የአገራችን አካባዎች የሚከበሩ የህዝብ እና ሐይማኖታዊ በዓላትን ማስተዋወቅ
- የአለም ቱሪዝም ቀን በማስመልከት ሁሉንም ክልሎች በማስተባበር የአገር ውስጥ ቱሪዝም ንቅናቄ እና የፕሮሞሽን ስራዎችን መስራት
- የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ለማሳደግ የሚያስችሉ ተከታታይ የውይይትመደረረኮችን ከተለየዩ ባለድርሻ አካለት ጋር ማድረግ።
- የጉብኝት ቁጠባ ሂሳብ (Guzo Saving Account) አጠናክሮ ማስተዋወቅና በተቀሩ የግል ባንኮች ማስጀመር፣
- የአገር ውስጥ ቱሪዝም የሚያስተዋውቁ የተለያዩ አይነት ፕሮሞሽናል ማቴሪያሎች በተለያዩ የአገር ውስጥ ቋንቋዎች ማዘጋጀት፣
- የአገር ውስጥ ጉብኝት ማበረታቻ ስርዓት ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ።
- የአገር ውስጥ ጎብኚዎችን የሚያነሳሳ ጋይድ ቡክ ማዘጋጀት፣
- የአገር ውስጥ ኹነቶች ካሌንድር (Event Calendar) ማዘጋጀትና ማስተዋወቅ፣
- ለአገር ውስጥ ቱሪዝም ማደግ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ድርጅቶች፣ ማህበራትና ግለሰቦች እውቅና መድረክ ማዘጋጀት።
- የስፖርት ቱሪዝምን በመጠቀም የአገር ውስጥ ቱሪዝም ንቅናቄ መፍጠር
- ተጽእኖ ፈጣሪ አገር ውስጥ ሁነቶች ስፖንሰር (Sponsoring events) በማድረግ የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ማስተዋወቅ፣

- የቱሪዝም መዳረሻዎችን የሚያስተዋውቅ ቢልቦርድ በተመረጡ የሀገራችን አካባቢዎች ማቆም (መትከል)፡፡

**6. በቱሪዝም ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻልና ልህቀትን ማረጋገጥ**

**ዋና ተግባር 1፡** የቱሪስት አገልግሎቶች ጥራትና ደረጃ ማሳደግ

**የሚጠበቅ ውጤት፡** የተሸሻለ የአገልግት ጥራትና ያደገ የጎብኝዎች እርካታ

**ዝርዝር ተግባራት**

- የሆቴሎችን ኮከብ ደረጃ ምደባ ማካሄድ
- የሎጅ፣ ሬስቶራንትና ደረጃ ምደባ ስታንዳርዶች በማዘጋጀት ማጸደቅ
- የቱሪስት አገልግት ሰጭ ተቋማን ብቃት ማረጋገጥ
- የባለኮከብ ሆቴሎች፣ ሎጆች፣ ሬስቶራንቶች እና አስጎብኚ ድርጅቶች የድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን ማከናወን
- የኢንቨስትመንትና ልዩ ልዩ ድጋፎችን መስጠት

**ዋና ተግባር 2፡ የዘርፉን የሰው ሃይል አቅምና ተወዳዳነት ማሳደግ**

**የሚጠበቅ ውጤት፡**

- የተሸሻለ የዘርፉ የሰው ሃይል አቅምና ሙያኝነት
- ያደገ በዘርፉ የተሰማረው የሰለጠነ የሰው ሃይል ሽፋንና ተወዳዳነት

**7. የዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢዎችን ጥበቃ ስራዎችን ማጎልበት**

**ዋና ተግባር 1፡ በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ አጠቃቀም ዙሪያ የህብረተሰብ ግንዛቤ ማሳደግ፣**

የሚጠበቅ ውጤት፡ ያደገ የህብረሰተሰብ ግንዛቤ

**ዋና ተግባር 2፡ በዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢዎች ላይ የህግ ማስከበር ሥራዎች ማሳደግ፣**

የሚጠበቅ ውጤት፡ የቀነሰ ህገ ወጥ ድርጊት

**ዋና ተግባር 3፡ በሰውና በዱር እንስሳት መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶችን መቀነስ እና አደጋዎችን የመከላከልና የመቆጣጠር ዝግጁነትን ማሳደግ፣**

የሚጠበቅ ውጤት፡

- የቀነሰ የሰውና የዱር እንስሳት ግጭት
- ያደገ የአደጋ መከላከልና ቁጥጥር አቅም

**ዋና ተግባር 4፡ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን አያያዝና አስተዳደርን ማጎልበት**

የሚጠበቅ ውጤት፡

- ያደገ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ቁጥርና የተፈጥሮ ይዞታቸው የተጠበቁ የዱር እንስሳት መኖሪያ አካባቢዎች
- ሥርዓተ ምህዳሩ ያልተናጋ/የተጠበቀ የዱር እንስሳት መኖሪያ አካባቢ

**ዋና ተግባር 5፡ የዱር እንስሳት ሃብቶች ዘላቂ አጠቃቃምን ማሳደግ**

የሚጠበቅ ውጤት፡ ከዱር እንስሳት ሃብቶች ያደገ ዘላቂ ተጠቃሚነት

**ዋና ተግባር 6፡ የዱር እንስሳት የጤና አገልግሎትን ማስፋፋት፣**

የሚጠበቅ ውጤት፡ የተሻሻለ የዱር እንስሳት ጤና አገልግሎት ተደራሽነት

**8. የቅርሶች ጥበቃ፣ እንክብካቤና ልማት ስራዎችን ማሳደግ**

**ዋና ተግባር 1፡ የቅርስ ምዝገባና አያያዝ ስራዎችን ማጎልበት**

የሚጠበቅ ውጤት፡ ያረገ የቅርስ ምዝገባ ሽፋንና ውጤታማ አስተዳደር

**ዋና ተግባር 2፡ የቅርሶች ጥበቃና እንክብካቤ ሥራዎችን ማሳደግ**

የሚጠበቅ ውጤት፡

- ✓ እሴታቸው በዘላቂነት የተጠበቀ ቅርሶች
- ✓ ቅርሶች ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት እንዲውሉ ማስቻል፤

**ዋና ተግባር 3፡ የቅርስ ጥናትና ሙዝየም አገልግሎትን ማጠናከር**

የሚጠበቅ ውጤት፡

- እሴታቸው ተጠብቆ የተያዙ ቅርሶች
- በዘላቂነት የለሙና ተደራሽ የሆኑ ቅርሶች

## 5. ስትራጅካዊ ግቦች፣ ዋና ተግባራት፣ ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾችና ዒላማዎች

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች | መለኪያ | የ2017 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2018 ዒላማ | የሩብ ዓመታት ዒላማዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| **1** | **ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት** | | | | | | | |
| **1.1** | **የዕቅድ ዝግጅት፣ የክትትልና ግምገማ አሰራር ማሻሻል** | | | | | | | |
| 1.1.1 | ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ ዕቅድና ሪፖርት ሰነድ ማዘጋጅት | በቁጥር | 5 | 5 | 2 | 1 | 1 | 1 |
| 1.1.2 | የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት | በቁጥር | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| **1.2** | **የቱሪዝም ስታቲስቲክስ ስርዓትን እና መረጃ አስተዳደርና አሰራርን ማሻሻል** | | | | | | | |
| 1.2.1 | የተሻሻለ የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት ስርዓት | በቁጥር | 1 | 1 | | | | 1 |
| 1.2.2 | የተከናወነ የቱሪዝም ሰርቬይ (Survey) | በቁጥር | 2 | 1 | | | | 1 |
| 1.2.3 | የተደራጀ የቱሪዝም መረጃዎች ዓይነት | በቁጥር | 4 | 5 | 1 | 1 | 1 | 2 |
| 1.2.4 | የዘርፉን መረጃ አያያዝ በቴክኖሎጂ በመደገፍ ማደራጀት | በመቶኛ | - | 80 | | 70 | 75 | 80 |
| **1.3** | **የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል** | | | | | | | |
| 1.2.1 | ግልጽነት የሰፈነበት የሰው ኃይል ስምሪት ማካሄድ በመቶኛ | በመቶኛ | 85 | 95 | 93 | 95 | 95 | 95 |
| 1.2.2 | ለአመራር እና ለሰራተኞች የሚሰጡ ሥልጠናዎችን ማሳደግ በቁጥር | በቁጥር | 15 | 15 | 1 | 5 | 5 | 4 |
| 1.2.3 | የውስጥ የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት | በቁጥር | 1 | | | | | 1 |
| 1.2.4 | የሰራተኛ እርካታን ማሳደግ | በመቶኛ | 85 | 90 | 85 | 87 | 90 | 90 |
| **1.4** | **የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል** | | | | | | | |
| 1.3.1 | የተመደበ በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል (ድርሻ) | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.3.2 | ነቀፌታ ያለበትን የኦዲት ግኝት መቀነስ | በመቶኛ | 5 | 5 | 1 | 2 | 2 | |
| 1.3.3 | የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ክፍያን ድርሻ ማሳደግ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.3.4 | የመንግስት ኤሌክትሮኒክስ ግዢን ድርሻ ማሳደግ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.3.5 | መሰረታዊ አገልግሎትን በቅልጥፍና በመስጠት የደንበኞችን እርካታ ማሻሻል | በመቶኛ | 90 | 95 | 90 | 92 | 93 | 95 |
| 1.3.6 | የንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም ማሻሻል | በመቶኛ | 70 | 85 | 73 | 75 | 80 | 85 |
| | | | | | | | | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች | መለኪያ | የ2017 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2018 ዒላማ | የሩብ ዓመታት ዒላማዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| **1.5** | **የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል** | | | | | | | |
| 1.4.1 | መረጃ ቋት ማደራጀት | በመቶኛ | 75 | 100 | 90 | 95 | 98 | 100 |
| 1.4.2 | በተቋሙ ወረቀት አልባ አሰራርን መተግበር | በመቶኛ | 80 | 90 | 80 | 83 | 85 | 90 |
| 1.4.3 | በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን አቶሜት ማድረግ | በመቶኛ | 85 | 95 | 80 | 85 | 90 | 95 |
| 1.4.4 | የተገልጋዮችን እርካታ ደረጃ ማሳደግ | በመቶኛ | 90 | 95 | 91 | 93 | 94 | 95 |
| 1.5.5 | የተዘረጋ በበይነ መረብ የታገዘ የጎብኝዎች ግብረ መልስ ስርዓት | በቁጥር | 1 | 1 | | 1 | | |
| 1.5.6 | የመዳረሻ መረጃዎች አያያዝና አስተዳደር ስርዓት (DMIS) | በቁጥር | - | 1 | | | 1 | |
| 1.5.7 | የቱሪዝም እሴት ሰንሰለትን ለማዘመን ተግባራዊ የተደረጉ የቴክሎሎጂ ውጤቶች | በቁጥር | - | 2 | | 1 | 1 | |
| 1.5.8 | ኔትወርክ የተዘረጋላቸው የጥበቃ ቦታዎች በቁጥር | በቁጥር | - | 2 | | 1 | 1 | |
| 1.5.9 | ኢንተርኔት የተሟላላቸው የጥበቃ ቦታዎች በቁጥር | በቁጥር | - | 9 | 2 | 2 | 2 | 3 |
| **1.6** | **የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል** | | | | | | | |
| 1.6.1 | የተመሰረተ የቱሪዝም መማክርት (Tourism Council) | በቁጥር | | 1 | | 1 | | |
| 1.6.2 | ከባለድርሻ አካላት ጋር የተካሄዱ የምክክር መድረኮች | በቁጥር | 10 | 12 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 1.6.3 | በቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ዘርፍ ማህበራት መካከል የተፈጠረ ውህደት | በቁጥር | - | 1 | | | 1 | |
| 1.6.4 | የተፈጠሩ የቱሪዝም ትስስሮች (ከሀገራት ጋር፣ ቀጠናዊ እና ዓለም አቀፋዊ) | በቁጥር | 12 | 10 | 2 | 3 | 3 | 2 |
| 1.6.1 | ለተቋም አቅም ግንባታ በሀገር ውስጥ አጋርነት የተገኘ ድጋፍ | በሚሊዮን ብር | 300,075. | 20 ሚሊዮን | 2 ሚሊዮን | 5 ሚሊዮን | 5 | 8 |
| 1.6.2 | ለተቋም አቅም ግንባታ በውጭ ሀገር አጋርነት የተገኘ ድጋፍ | በሚሊዮን ብር | 25 | 50 ሚሊዮን | - | 30 | 10 | 10 |
| 1.6.3 | መረጃዎችን በተለያዩ የተግባቦት ዘዴዎች ተደራሽ ማድረግ | በመቶኛ | 88 | 90 | 88 | 88 | 90 | 90 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች | መለኪያ | የ2017 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2018 ዒላማ | የሩብ ዓመታት ዒላማዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| **1.7** | **ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል ማሻሻል** | | | | | | | |
| 1.6.1 | የተጠሪ ተቋማት ዕቅድን ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና ማጣጣም | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | | | |
| 1.6.2 | የየሩብ ዓመት የተጠሪ ተቋማት ሪፖርት መገምገም | በቁጥር | 3 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 1.6.3 | የክልሎችን ዕቅድ ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና ማጣጣም | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | | | |
| 1.6.4 | በየሩብ ዓመት ከክልሎች ጋር የዘርፍ አፈጻጸም በጋራ መገምገም | በቁጥር | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 1.6.5 | ለክልሎች ወቅታዊ የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት | በቁጥር | 9 | 15 | 1 | 5 | 5 | 4 |
| **1.6** | **የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና የክትትል ሥራዎችን ማሻሻል** | | | | | | | |
| 1.6.1 | በብልሹ አሰራር ዙርያ ጥቆማ ከተደረገባቸው ውስጥ ማስተካከያ የተደረገባቸው | በመቶኛ | 100 | 100 | 70 | 80 | 90 | 100 |
| 1.6.2 | ለብልሹ አሰራር የተጋለጡ አሰራሮች በጥናት በመለየት የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብ | በቁጥር | 5 | 5 | 1 | 2 | 1 | 1 |
| 1.6.3 | የሀብት ምዝገባ ያካሄዱ አመራሮች እና ባለሞያዎች ድርሻ ማሳደግ | በመቶኛ | 90 | 100 | 90 | 95 | 100 | 100 |
| 1.7 | **የሴቶችና ማሕበራዊ ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ማሻሻል** | | | | | | | |
| 1.7.1 | የህጻናት ማቆያ አገልግሎት ተጠቃሚ ሴት ሰራተኞች ብዛት ማሳደግ | በቁጥር | 3 | 5 | - | - | - | 5 |
| 1.7.2 | ወደ አመራር የመጡ ሴት ሰራተኞች ብዛት ማሳደግ | በቁጥር | 8 | 12 | 2 | - | - | 2 |
| 1.7.3 | ሥልጠና ያገኙ ሴት ሰራተኞች ድርሻ ማሳደግ | በመቶኛ | 40 | 50 | 42 | 43 | 45 | 50 |
| 1.7.4 | ለአካል ጉዳተኛ ሰራተኞችና ተገልጋዮች ምቹ የስራ ሁኔታና ቦታ መፍጠር | በመቶኛ | 70 | 80 | 72 | 74 | 76 | 80 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች | መለኪያ | የ2017 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2018 ዒላማ | የሩብ ዓመታት ዒላማዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| **1.8** | **የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎችን ማሻሻል** | | | | | | | |
| 1.8.1 | የአረንጓዴ አሻራ ተግባራትን ማካሄድ/ችግኞችን መትከል | በቁጥር | 213,247 | 400 ሺ. | 330 ሺ. | 70 ሺ. | | |
| 1.8.2 | የአቅመ ደካማ ማህበረሰቦች የመኖሪያ ቤቶች መገንባት | በቁጥር | 6 | 12 | 5 | 7 | | |
| 1.8.3 | የአቅመ ደካማ ማህበረሰቦች የመኖሪያ ቤቶች መገንባት | በብር | 2 ሚሊዮን | 8.4 ሚሊዮን | 4.2 ሚሊዮን | 4.2 ሚሊዮን | | |
| 1.8.4 | የአቅመ ደካማ ቤተሰብ ተማሪዎች ድጋፍ | በቁጥር | 300 | 1666 | 1666 | | | |
| 1.8.5 | የአቅመ ደካማ ቤተሰብ ተማሪዎች ድጋፍ | በብር | 1.2 ሚሊዮን | 3 ሚሊዮን | 3 ሚሊዮን | | | |
| 1.8.6 | ለተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶች የተደረገ ድጋፍ | በብር | 3 ሚሊዮን | 2 ሚሊዮን | 2 ሚሊዮን | | | |
| 1.8.7 | የተደረገ ደም ልገሳ (ድርሻ ከሰራተኛ ብዛት) | በመቶኛ | 30 | 70 | 30 | 35 | 40 | 70 |
| 1.8.8 | ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናትን መደገፍ | በቁጥር | 5 | 5 | | | | 5 |
| 1.8.9 | ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናትን መደገፍ | በብር | 60,000 | 240,000 | | | | 240,000 |
| 2 | **የሀገሪቱን የቱሪዝም አለኘታዎች በመለየት መዳረሻዎችን ማልማትና ማስፋፋት** | | | | | | | |
| 2.1 | **የሀገሪቱን የቱሪዝም አለኘታዎች መለየት፣ አዳዲስ መዳረሻዎችን ማልማት** | | | | | | | |
| **2.1.1** | ለተግባራዊነት የተዘጋጁ የቱሪዝም መዳረሻ ልማት ፕሮጀክቶች | በቁጥር | 7 | 5 | | 2 | 2 | 1 |
| **2.1.2** | የተከናወነ አገር አቀፍ የሀብት ልየታ ስራ (Tourism Resources Mapping) | በቁጥር | 1 | 1 | | 1 | | |
| **2.1.3** | የለሙ አዳዲስ የቱሪዝም መዳረሻዎች | በቁጥር | 6 | 11 | 1 | 4 | 5 | 1 |
| **2.1.4** | የተተገበረ ሀገር አቀፍ የቱሪዝም መዳረሻዎች ስታንዳርድ | በቁጥር | - | 1 | | 1 | | |
| 2.1.5 | ሀገር አቀፍ የመዳረሻ ተወዳዳሪነት ስታንዳርዶችን ያሟሉ መዳረሻዎች | በቁጥር | 26 | 40 | 9 | 9 | 10 | 12 |
| **2.2** | **በነባር የቱሪዝም መዳረሻዎች ላይ እሴት በመጨመር ተወዳዳሪነታቸውን ማሳደግ** | | | | | | | |
| 2.2.1 | የኢትዮጵያ ዓለም አቀፋዊ የቱሪዝም ተወዳዳሪት ደረጃን ማሻሻል | - | 110ኛ | | | | | 110ኛ |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.2.2 | እሴት የተጨመረባቸው ነባር የቱሪዝም መዳረሻዎች | በቁጥር | 13 | 20 | | 5 | 10 | 5 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች | መለኪያ | የ2017 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2018 ዒላማ | የሩብ ዓመታት ዒላዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| 2.2.2 | ልዩ ፍላጎትን (Niche Tourism Products) መሰረት ያደረጉ የቱሪዝም ምርቶች ዓይነት | በቁጥር | 5 | 5 | 1 | 1 | 2 | 1 |
| **2.3** | **የቱሪዝም መሰረተ ልማትን ማስፋፋት** | | | | | | | |
| 2.3.1 | አዳዲስ መሰረተ ልማት የተሟላላቸው መዳረሻዎች (መስህቦች) | በቁጥር | 5 | 10 | 1 | 4 | 4 | 1 |
| 2.3.2 | በቱሪስት መደራሻዎች የተደረጉ የመሰረተ ልማት ማሻሻያዎች | በቁጥር | 9 | 20 | 1 | 7 | 10 | 2 |
| **2.4** | **የቱሪስት ምርቶች ዓይነትና ደረጃ ማሳደግ** | | | | | | | |
| 2.4.1 | የተለዩ እና ለገበያ ዝግጁ የሆኑ የቱሪስት ምርቶች ዓይነት (tourist commodities) | በቁጥር | 5 | 5 | 1 | 1 | 2 | 1 |
| 2.4.2 | ስታንዳርድ የወጣላቸው የቱሪስት ምርቶች | በቁጥር | 3 | 5 | | 1 | 2 | 2 |
| 3 | **የዘርፉን የፋይናንስ አቅም በማጎልበት ኢንቨስትመንት ማስፋፋትና የሚፈጠሩ የስራ እድሎችን ማሳደግ** | | | | | | | |
| 3.1 | **የሀገር ውስጥ እና የውጭ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋትና ማሳደግ** | | | | | | | |
| 3.1.1 | የኢንቨስትመንት እድሎችን ለማስተዋወቅና ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ የተካሄደ ፎረም | በቁጥር | - | 1 | | 1 | | |
| 3.1.2 | ያደገ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች ቁጥር | በቁጥር | 228 | 400 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 3.1.3 | ያደገ የውጭ ባለሃብቶች ቁጥር | በቁጥር | - | 15 | 2 | 3 | 5 | 5 |
| 3.1.4 | የኢንቨስትመንት ፈቃድ የወሰዱ/የተመዘገቡ ባለሃብቶች ቁጥር | በቁጥር | - | 415 | 102 | 103 | 105 | 105 |
| 3.1.6 | ያደገ አዳዲስ የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ብዛት | በቁጥር | 64 | 100 | 20 | 30 | 30 | 20 |
| 3.1.7 | ድጋፍ የተደረገላቸው ባለሃብቶች | በቁጥር | 434 | 635 | 150 | 168 | 167 | 150 |
| 3.1 | ደረጃቸውን የጠበቁ የመኝታ ክፍሎች ብዛት | በቁጥር | 1743 | 2,500 | 550 | 650 | 650 | 650 |

| | ስትራቴጅክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች | መለኪያ | የ2017 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2018 ዒላማ | የሩብ ዓመታት ዒላዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| **3.2** | **በዘርፉ የሚፈጠሩ የስራ እድሎችን ማሳደግ** | | | | | | | |
| 3.2.1 | በዘርፉ የተፈጠረ ቀጥተኛ የሆነ የስራ እድል | በቁጥር | 127,456 | 150,000 | 20000 | 30000 | 50000 | 50000 |
| **3.3** | **የፋይናንስ አማራጮችን ማስፋት** | | | | | | | |
| 3.3.1 | የተዘረጋ የቱሪዝም ፈንድ አሰባሰብ ስርዓት | በቁጥር | - | 1 | | | 1 | |
| 3.3.2 | የቱሪዝም ፈንድ ምንጮች ዓይነት | በቁጥር | - | 5 | 1 | 1 | 2 | 1 |
| **4** | **የአለም አቀፍ ፕሮሞሽንና ግብይት ስራዎችን በማጎልበት የጎብኚዎች ፍሰትና የውጪ ምንዛሬ ገቢን ማሳደግ** | | | | | | | |
| **4.1** | **ውጤታማ አለም አቀፍ ፕሮሞሽን ስራዎችን በማጎልብት የገበያ ድርሻና የቱሪስት ፍሰትን ማሳደግ** | | | | | | | |
| 4.1.1 | ተሳትፎ ተደረገባቸው አገርን የማስተዋወቂያ መድረኮች (trade fairs Expos & Road Shows) | በቁጥር | 10 | 10 | - | 4 | 3 | 3 |
| 4.1.2 | የተፈጠሩ የገበያ ትስስሮች (B2B) | በቁጥር | 70 | 100 | - | 30 | 30 | 40 |
| 4.1.3 | የተከናወኑ ብራንድ ካምፔይኖች | በቁጥር | 16 | 20 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 4.1.4 | የተቀረፁ የከተሞችና መዳረሻዎች ብራንድ | በቁጥር | 2 | 4 | | 1 | 2 | 1 |
| 4.1.5 | በሚሲዮኖች የተቋቋሙ ቋሚ የቱሪዝም ማስተዋወቂያና መረጃ መስጫ ማዕከላት (ስርዓት) | በቁጥር | - | 15 | - | 7 | 6 | 2 |
| 4.1.6 | ኢትዮጵያን ለማስተዋወቅ በውጭ ሀገራት የተዘጋጁ ሁነቶች | በቁጥር | - | 7 | 1 | 2 | 2 | 2 |
| 4.1.7 | ያደገ የገበያ ድርሻ | በመቶኛ | - | 2 | | | | 2 |
| 4.1.8 | አዲስ የተፈጠሩ አዳጊ ገበያዎች | በቁጥር | 1 | 2 | | | 1 | 1 |
| 4.1.9 | የቱሪስት ፍሰት መጠን በሚሊዮን | በቁጥር | 1,295,372 | 1,564,586 | 250,000 | 459,368 | 405,218 | 350,000 |
| 4.1.10 | የውጪ ምንዛሬ ገቢ በቢሊዮን ዶላር | በቁጥር | 4.8 | 7.6 | 0.938 | 1.72 | 1.52 | 1.3 |
| **4.2** | **የቱሪስት መረጃ ማዕከላት አገልግሎቶች ደረጃ እና የመረጃ ተደራሽነት ማሻሻል** | | | | | | | |
| 4.2.1 | የቱሪስት መረጃ ማዕከላት ተገልጋዮች ቁጥር | በቁጥር | 184,925 | 340,367 | 82431 | 82431 | 82591 | 82914 |
| 4.2.2 | ያደገ የቱሪስት መረጃ ጥራት | በቁጥር | 80 | 90 | - | - | - | 90 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች | መለኪያ | የ2017 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2018 ዒላማ | የሩብ ዓመታት ዒላማዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| **4.3** | **ጠንካራ የዲጂታል ፕሮሞሽንና ማርኬቲንግ አሰራር በመተግበር የኦን ላየን ሽፋን ማሳደግ** | | | | | | | |
| 4.3.1 | ያደገ የማህበራዊ ሚዲያ የኦን ላየን ሽፋን በመቶኛ | በመቶኛ | 70 | 80 | 72 | 74 | 76 | 80 |
| 4.3.2 | ያደገ የዲጂታል ክፍያ ስርዓት | በመቶኛ | - | 100 | 50 | 70 | 80 | 100 |
| **4.4** | **MICE ቱሪዝምን እና ስቶፐኦቨር ቱሪዝምን ማሳደግ** | | | | | | | |
| 4.4.1 | በኢትዮጵያ የተካሄዱ አለም አቀፍ ኹነቶች | በቁጥር | 117 | 120 | 20 | 40 | 40 | 20 |
| 4.4.2 | ፕሮፌሽናል ኹነት አዘጋጅ ድርጅቶች (PCOs) | በቁጥር | - | 45 | - | 15 | 15 | 15 |
| 4.4.3 | የጨመረ የቢዝነስ ቱሪስቶች መጠን | በፐርሰንት | - | 35 | 40 | | | 40 |
| 4.4.4 | የተተገበሩ የMICE ቱሪዝም ማስታወቂያ ፓኬጅ | በቁጥር | - | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 4.4.5 | የተተገበሩ የስቶፐኦቨር ቱሪዝም ማስታወቂያ ፓኬጅ | በቁጥር | - | 1 | | 1 | | |
| 4.4.6 | የስቶፐኦቨር ጎብኚዎች መጠን | በቁጥር | - | 75,000 | 10000 | 20000 | 20000 | 25000 |
| **5** | **የአገር ውስጥ ቱሪዝምን በማጎልበት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅዖ ማሳደግ** | | | | | | | |
| **5.1** | **የጉብኝት ባህልን በማሻሻል የአገር ውስጥ ቱሪዝም ማሳደግ** | | | | | | | |
| 5.1.1 | የተካሄዱ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች | በቁጥር | 25 | 30 | 5 | 10 | 10 | 2 |
| 5.1.2 | የተዘጋጀ ሀገር አቀፍ የቱሪዝም ኤግዚቢሽን | በቁጥር | - | 1 | | 1 | | |
| 5.1.3 | ሀገር አቀፍ ኤግዚቢሽኑን የጎበኙ ሰዎች | በቁጥር | - | | | | | |
| 5.1.4 | የተመሰረቱ የጉብኝት ክበባት | በቁጥር | 150 | 450 | 100 | 100 | 100 | 150 |
| 5.1.5 | የተካሄዱ የአገር ውስጥ ቱሪዝም ካምፔኖች | በቁጥር | 7 | 10 | 2 | 3 | 3 | 2 |
| 5.1.6 | የአገር ውስጥ ጎብኚ መጠን | በሚሊዮን | 48.3 | 51.4 | 15 | 14 | 13 | 9.4 |
| 5.1.7 | የአገር ውስጥ ቱሪዝም ገቢ በቢሊዮን | በብር | 77.2 | 82 | 19.2 | 24 | 24 | 15 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች | መለኪያ | የ2017 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2018 ዒላማ | የሩብ ዓመታት ዒላዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| 6 | **በቱሪዝም ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻልና ልህቀትን ማረጋገጥ** | | | | | | | |
| 6.1 | **የቱሪስት አገልግሎቶች ጥራትና ደረጃ ማሳደግ** | | | | | | | |
| 6.1.1 | በደረጃ የተመደቡ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት | በቁጥር | 154 | 150 | 50 | 50 | 50 | |
| 6.1.2 | ክትትልና ቁጥጥር የተደረገባቸው የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች | በቁጥር | 196 | 200 | 50 | 50 | 50 | 50 |
| 6.1.3 | ብቃታቸው ተረጋግጦ እውቅና የተሰጣቸው አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች | በቀጥር | 530 | 550 | 150 | 150 | 150 | 100 |
| 6.1.4 | የጥራት አመራር ስርዓት /Total Quality management system/ ተግባራዊ ያደረጉ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች | በቁጥር | - | 100 | | | 50 | 50 |
| 6.1.5 | ያደገ የጎብኝዎች እርካታ | በመቶኛ | - | 75 | | | | 75 |
| 6.2 | **የዘርፉን የሰው ሃይል አቅምና ተወዳዳነት ማሳደግ** | | | | | | | |
| 6.2.1 | የሙያ እውቅና የተሰጣቸው (Professionally Certified) የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ሙያተኞች | በቁጥር | - | 500 | 50 | 100 | 150 | 200 |
| 6.2.2 | የአጭር ጊዜ ስልጠና ያገኙ ባለሙያዎች/የሰው ሃይል | በቁጥር | - | 200,000 | 50000 | 50000 | 50000 | 50000 |
| 6.2.3 | በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሃይል ሽፋን | በመቶኛ | 44 | | | | | 49 |
| 7 | **የዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢዎችን ጥበቃ ስራዎችን ማጎልበት** | | | | | | | |
| 7.1 | **በዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ስራዎች የህብረተሰብ አጋርነትንና ተሳትፎ ማጎልበት** | | | | | | | |
| 7.1.1 | በአማራጭ የኑሮ ዘይቤ ተጠቃሚ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች | በቁጥር በሺ.ህ | 43,465 | 50 | 10 | 15 | 15 | 10 |
| 7.1.2 | ተጠቃሚ የሆኑ የማህበር አባላት | በቁጥር | 6,430 | 3,500 | 750 | 1200 | 1200 | 350 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች | መለኪያ | የ2017 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2018 ዒላማ | የሩብ ዓመታት ዒላዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| 7.1.3 | በገፅ ለገፅ ግንዛቤ የተሰጠው የህብረተሰብ ክፍል | በቁጥር | 211,950 | 220,000 | 50,000 | 65,000 | 65,000 | 40,000 |
| 7.1.4 | በሚዲያ ግንዛቤ የተፈጠረላቸው ዜጎች | በቁጥር | 9.3 | 10.012 | 3 | 3 | 3 | 1.012 |
| **7.2** | **በዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢዎች ላይ የሕግ ማስከበር ሥራዎችን ማሳደግ** | | | | | | | |
| 7.2.1 | የቀነሱ ህገወጥ ድርጊቶች | በመቶኛ | 73.1 | 82 | | | | 82 |
| | | | | | | | | |
| 7.2.3 | የተካሄዱ የጥበቃና ቁጥጥር ሥራዎች | በሺ.ህ ሰው ሰዓት | 2092.0 | 2,158 | 539 | 540 | 540 | 539 |
| 7.2.4 | የተቀናጀ የጥበቃና ክትትል ስራዎች | በቁጥር | 41 | 14 | | 4 | 5 | 5 |
| 7.2.5 | በአነፍናፊ ውሻ እገዛ የተካሄደ የዱር እንስሳት ውጤቶች ህገወጥ ዝውውርና ቁጥጥር | በቁጥር | 38 | 128 | 32 | 32 | 32 | 32 |
| 7.2.6 | በዱር እንስሳት ወንጀል በተጠረጠሩ ቦታዎች የተካሄደ የሰርቬላንስ ስራ | በቁጥር | 34 | 2 | 1 | | 1 | |
| 7.2.7 | ለኢንቫይሮመንታል ክራይም ዩኒት የተደረገ ድጋፍ | በቁጥር | 2 | 2 | | 1 | | 1 |
| **7.3** | **በዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢያቸው ላይ የሚደርሱ አደጋዎችንና ግጭቶችን የመከላከልና የመቆጣጠር ዝግጁነትን ማሳደግ** | | | | | | | |
| 7.3.1 | ያደገ የአደጋ መከላከልና ቁጥጥር አቅም | በመቶኛ | 62 | 73 | | | | 73 |
| 7.3.2 | በጥበቃ ቦታዎች የተቋቋመ የእሳት ብርጌድ | በቁጥር | 1 | 1 | | 1 | | |
| 7.3.3 | የተገነባ የእሳት መከላከያ ብሬክ (Fire Break) | በቁጥር | 91.6 | 30 | | | 30 | |
| **7.4** | **የዱር እንስሳት ጥናትና ምርምር እና የጤና አገልግሎትን ማስፋፋት፣** | | | | | | | |
| 7.4.1 | ያደገ የዱር እንስሳት ጤና አገልግሎት ሽፋን | በመቶኛ | 69 | 73 | 69.5 | 71 | 72 | 73 |
| 7.4.2 | የተከናወኑ የጥናትና ቆጠራ ስራዎች (በራስ አቅምና በትብብር) | በቁጥር | 22 | 31 | 4 | 12 | 9 | 6 |
| 7.4.3 | ጥቅም ላይ የዋሉ የጥናትና ምርምር ውጤቶች | በቁጥር | 22 | 23 | | 4 | 9 | 10 |
| | | | | | | | | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች | መለኪያ | የ2017 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2018 ዒላማ | የሩብ ዓመታት ዒላዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| 7.4.4 | ወሳኝ በሆኑ የዱር እንስሳትዝርያዎች ላይ የተካሄዱ ሀገር አቀፍ ቆጠራ (Census) | በቁጥር | 1 | 1 | | | 1 | |
| 7.4.5 | የመጥፋት አደጋ በተጋረጠባቸው የዱር እንስሳት ዝርያዎች የተካሄደ ቆጠራ ((Ethiopian wolf, wild ass and cheetah) | በቁጥር | 1 | 1 | | 1 | | |
| | | | | | | | | |
| 7.4.7 | የዱር እንስሳት በሽታ ስርጭትን ለመከላከል የተካሄደ ቁጥጥር | በቁጥር | 7 | 7 | | | 4 | 3 |
| 7.4.7 | ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል በቤት እንስሳት ላይ የተካሄደ ክትባት | በቁጥር | 55,907 | 250,000 | | | 250,000 | |
| 7.5 | **የዱር እንስሳትና ጥበቃ ቦታዎችን ማጅመንት ማሳደግ** | | | | | | | |
| 7.5.1 | ያደገ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን ሽፋን | በመቶኛ | 10.24 | 10.06 | | | | 10.06 |
| 7.5.2 | አዲስ የተቋቋሙ ጥበቃ ቦታዎች | በቁጥር | 2 | 2 | | | 2 | |
| 7.5.4 | የተዘረጋ የድንበር ዘለል የጥበቃ ቦታዎች የጋራ ሥርዓት አያያዝና ሥነ ምህዳራዊ ትስስር | በቁጥር | 1 | 1 | | | | 1 |
| 7.5.6 | በIUCN እውቅና ያገኙ ጥበቃ ቦታዎች | በቁጥር | 0.8 | 4 | | | 4 | |
| 7.5.7 | ያገገሙ የስነ-ምህዳር ቦታዎች/የዱር እንስሳት መኖሪያ ስፍራዎች | በቁጥር | 50 | 50 | | | 50 | |
| 7.5.8 | የተወገደ መጤ የእፅዋት ዝርያዎች | በሄክታር | 103.25 | 500 | | 200 | 300 | |
| 7.5.9 | በመጥፋት አደጋ የተደቀነባቸውን የዱር እንስሳት ዝርያዎች የማራቢያ ማዕከል (semi-insitu captive breeding for endangered species) | በቁጥር | - | 1 | | | | 1 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች | መለኪያ | የ2017 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2018 ዒላማ | የሩብ ዓመታት ዒላዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| 7.6 | **በዱር እንስሳት ሃብቶችን ዘላቂ አጠቃቀም ማሳደግ** | | | | | | | |
| 7.6.1 | ከፍጆታዊ አጠቃቀም የተገኘ ገቢ | በሚሊዮን | 160 | 215 | 5 | 55 | 100 | 55 |
| 7.6.2 | ከኢ-ፍጆታዊ አጠቃቀም የተገኘ ገቢ | በሚሊዮን | 35.4 | 135 | 1 | 10 | 65 | 59 |
| 7.6.3 | የካርበን ክምችት በጥበቃ ቦታዎች (Measured sequestration of carbon in PAs) | በቁጥር | 1 | 1 | | | 1 | |
| 8 | **የቅርሶች ጥበቃና ልማት ሥራዎችን ማሳደግ** | | | | | | | |
| 8.1 | **የቅርስ ምዝገባና አስተዳደር ስራዎችን ማጠናር** | | | | | | | |
| 8.1.1 | የተመዘገቡ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች | ቁጥር | 1,140 | 1,200 | 100 | 400 | 400 | 300 |
| 8.1.2 | የተመዘገቡ ቋሚ ቅርሶች | | 439 | 200 | 50 | 50 | 50 | 50 |
| 8.1.3 | በቋሚና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ላይ የተካሄደ የቁጥጥር ስራ | ቁጥር | 517 | 570 | - | 210 | 360 | - |
| 8.1.4 | በUNESCO ወካይ ቅርስነት ለማስመዝገብ የተዘጋጁ ማስመረጫ ሰነዶች | በቁጥር | 2 | 2 | | 1 | 1 | |
| 8.1.5 | በUNESCO የተመዘገቡ ቅርሶች | ቁጥር | 2 | 1 | | | | 1 |
| 8.1.6 | ለሀገር ቀአፍ እና ዓለም አቀፍ ቅርሶች የተዘጋጀ የቀርስ አስተዳደር እቀድ (Management Plan) | በቁጥር | 2 | 1 | | | | 1 |
| 8.1.7 | ክለላ (Delineated) የተደረገላቸው መካነ ቅርሶች | | | | | | | |
| **8.2** | **የቋሚና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ጥበቃና እንክብካቤ ስራዎችን ማጠናከር፤** | | | | | | | |
| 8.2.1 | ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገላቸው ቋሚ ቅርሶች | ቁጥር | 13 | 17 | - | 1 | 6 | 10 |
| 8.2.2 | ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገላቸው ተንቀሳቃሽ ቅርሶች | በቁጥር | 2,088 | 1,816 | 454 | 454 | 454 | 454 |
| | | | | | | | | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች | መለኪያ | የ2017 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2018 ዒላማ | የሩብ ዓመታት ዒላዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| **8.3** | **የቅርስ ጥናትና የሙዚየም አገልግሎትን ማላቅ** | | | | | | | |
| 8.3.1 | በቅርስ ላይ የተከናወኑ ሳይንሳዊ ጥናቶች | በቁጥር | 10 | 9 | - | 3 | 3 | 3 |
| 8.3.2 | የታተሙ ጥናቶች | በቁጥር | 2 | 3 | | | | 3 |
| 8.3.3 | የኮምፓራቲቭ አናቶሚ ስብስብና ኤግዚቢሽን | በቁጥር | 125 | 250 | 25 | 100 | 100 | 25 |
| 8.3.4 | የጨመረ ሙዚየም ብዛት | በቁጥር | 2 | 1 | | | | 1 |
| 8.3.5 | ለዕይታ የቀረቡ ጊዜያዊ ዐውደ-ርእይ | በቁጥር | 2 | 2 | | 1 | | 1 |
| 8.3.6 | በአገር አቀፍ ስታንዳርዶች ደረጃ የወጣላቸው ሙዝየሞች | በቁጥር | 4 | 3 | 2 | | | 1 |
| 8.3.7 | የቅርስ ጥናትና ምርምር የላቦራቶሪ አገልግሎት መስጠት | በቁጥር | 172 | 150 | 25 | 50 | 50 | 25 |
| | በአገር አቀፍ ደረጃ የጋራ መገለጫ የሆኑ የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶችን የምርምር ሰነድ ማዘጋጀት | በቁጥር | 1 | 1 | | | | 1 |

## 6. የእቅዱ ማስፈፀሚያ ስልቶች

ይህን እቅድ ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉት ማፈፀሚያ ስልቶች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

- **የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም መገንባት**
    - ✓ የሴክተርና የተቋም ትራንስፎርሜሽን ወይም ለዉጥ ማከናወን፣
    - ✓ የፖሊሲና  የህግ መሻሻያዎች ማከናወን፣
    - ✓ በአገልግሎት ሠጪ ተቋማት የተሠማሩ ባለሙያዎችን በአጫጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ስልጠናዎች በማብቃት የአገልግሎት አሠጣጡን ማላቅ፣
    - ✓ አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን ማስፋት፣
    - ✓ የዘርፍ (የሙያና የንግድ ማህበራት) አደረጃጀቶችን ማጠናከር፣
    - ✓ የዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ፣ የመረጃ አያያዝ ስርዓቱ በቴክኖሎጂ ማዘመን፣ ዘመናዊና ለአጠቃቀም ምቹ የሆኑ መተግበሪያዎችን /Application/ ማልማት፣
- **የዘርፉ ተዋናዮች መካከል ትስስር ማጠናከር እንዲሁም ከአጋርና ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሠራሮችን ማጠናከር፣**

የተዘርፉ ተዋናዮች ቅንጅታዊ አሠራሮችን ለማጠናከር ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ጉዳዮች ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡-

- ✓ ከጥናትና ምርምር ተቋማት (ከመካናተ ትምህርት ጋር ትስስርን ማስፋት)፣
- ✓ ከመ.ያ.ዶች ጋር ትስስርን ማጠናር፣
- ✓ የግል ዘርፉን ቁመና በአሰራር መደገፍና ማጠናከር፣
- ✓ በዘርፉ ያሉ አራቱን ተዋናዮች የግል ቁመና ማጠናከር እንዲሁም እርስ በእርስ ያላቸውን ትስስር ማጎልበት፣
- ✓ የሀገር ሀብትን በአግባቡ ሥራ ላይ ከማዋል አንፃር ቅንጅታዊ አሠራሮችን ማጎልበት፣
- ✓ ከሌሎች ሀገራት እና ቀጠናዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የስራ ግንኙነትንና ትስስርን ማጠናከር

- **የማህበረሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማጠናከር**
  - ✓ በቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችና መስህቦች ለሚገኙ ማህበረሰቦች በቅርስ ጥበቃና በተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና እንክብካቤ ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማስቻል፤
  - ✓ የቱሪዝም ሃብቶች ባለቤት የሆነው ህብረተሰብ የባለቤትነት ስሜቱ እንዲጎለብት በማድረግ ሃብቶቹን እንዲጠብቅና እንዲንከባከብ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር በቱሪዝም ልማት ውስጥ የተደራጀ ተሳትፎ እንዲያደርግ እና የጥቅሙ ተካፋይ እንዲሆን ማስቻል፡፡
  - ✓ ማህበረሰብ ተኮር የቱሪዝም እንቅስቃሴ ለማካሄድና ዘላቂ የቱሪዝም ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አሰራሮችንና ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ማድረግ፡፡
- **በዘርፉ ልማት ውስጥ የግል ዘርፉን ሚና ማሳደግ፣**

  በዚህ ስር ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች፡-

  - ✓ በዘርፉ የባለሀብቱን ተሳትፎ ለማጎልበት የሚያግዙ ምቹ አሰራሮችን መፍጠር
  - ✓ የመንግስትና የግል ዘርፍ ሽርክናን ለማጎልበት የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓቶችን መዘርጋት፣
  - ✓ አማራጭ የሥራ ዘርፎችን መለየትና እንዲተገበሩ ድጋፍ መስጠት፣
  - ✓ የመንግስትን እና የግሉን ዘርፍ አጋርነት ማጠናከር፣

የዘርፉን የልማት እቅድ በህብረተሰቡና በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ተግባራዊ በማድረግና የተጣሉትን ግቦች ስኬታማ በማድረግ ለሀገራዊ ራዕይ መሳካት የድርሻውን በመወጣት በእቅድ ዘመኑ የሚከተሉት የክትትል፣ ግምገማና የድጋፍ አቅጣጫዎች በስራ ላይ የሚውሉ ይሆናል::

## 6.1 የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት

- በዘርፉ መሪ የልማት ዕቅድ ዙሪያ ከክልሎችና ከማህበራት ጋር በመወያየት ግብዓት ማሰባሰብ እና የጋራ መግባባት ላይ መድረስ፣
- በእቅዱ ዙሪያ ኦርንቴሽን በአመት ሁለት ጊዜ መስጠት
- የእቅድ አፈጻጸም የክትትል ቼክ ሊስት ይዘጋጃል፡፡ በሶፍት ዌር የታገዘ ስርዓት እንዲኖር ይደረጋል፡፡
- የክትትልና ግምገማ የአሰራር ሥርዓት ማዘጋጀትና አጸደቆ ተግባራዊ ማድረግ፡፡
- የመካከለኛ ዘመንና አመታዊ የልማት እቅዶችን በየደረጃው በማዘጋጀት ተግባራዊ መሆናቸውን መከታተል፣

- ተጠሪ ተቋማት ተልዕኮቻቸውን በአግባቡ እንዲወጡ መደገፍና መከታተል፡፡
- የሪፖርት ግንኙነትን በኦንላይን ማከናዎን

## 6.2 የግምገማና ግብረ መልስ ሥርዓት

- የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በየ ወሩና እንደአስፈላጊነቱ ባጠረ ጊዜ (የሩብ ዓመት፣ የ6 ወራት፣ የ9 ወራትና ዓመታዊ አፈጻጸም) ቀርቦ ይገመገማል፡፡
- ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ይዘረጋል፡፡
- የተከናወኑ የተቋሙን ሪፖርቶች ዲጅታላይዝ በሆነው የሪፖርት ማቅረቢያ ሶፍት ዌር በመጫን ለሚመለከታቸው እንዲደርስ ይደረጋል::
- የሴክተር ዕቅድ አፈፃፀም ጉባኤ ለባለድርሻ አካላት ቀርቦ ይገመገማል፡፡
- በየደረጃው የሚገኙ ባለድርሻ አካላት በመስክ በመገኘት የእቅድ አፈፃፀም ሂደቱ እንዲከታተሉና እንዲገመግሙ ድጋፍ ማድረግ፣

የጽሁፍ ግብረ-መልስ ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት ይሰጣል፡፡ እንዲሁም አስፈላጊ በሆኑ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በአካል መስክ ምልከታ ሊደረግ ይችላል፡፡ ጠንካራ አፈጻጸም የተለዩ ተቋማት፣ ክልሎች እና ግለሰቦች እውቅና ይሰጣል::